ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 238 ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ ዳኜ አበራ

## ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን ችግሮችን ተጋፍጠን ለማሸነፍ መነጋገር፣ መግባባትና አቅጣጫችንን አስተካክለን መጓዝ ይኖርብናል››

### - ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- እኛ ኢትዮጵያውያን ችግሮችን ተጋፍጠን ለማሸነፍ መነጋገር፣ መደጋገፍ፣ መግባባትና አቅጣጫችንን አስተካክለን መጓዝ ይኖርብናል ሲሉ የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንትና የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የበላይ ጠባቂ ሳህለወርቅ ዘውዴ 81ኛው የኢትዮጵያ አርበኞች ድል መታሰቢያ በዓል ትናንት ሲከበር እንደገለጹት፤እኛ ኢትዮጵያውያን ችግሮቻችንን ተጋፍጠን ለማሸነፍ መነጋገር፣ መግባባትና አቅጣጫችንን አስተካክለን መጓዝ ይኖርብናል።ሰላም የሰፈነባት የለማች ኢትዮጵያን ለቀጣይ ትውልድ ለማውረስ የድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

በመልካም ለመታወስ፣ ልጆቻችን የማያፍሩባት፣ ሰላም የሰፈነባትና የለማች አገር ለማውረስ የድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤የተሻለ ሃሳብ ካለን ስናቀርብ፣ ስንቀበል፣ በሃሳብ ስንከራከር፣ ካልተቀበልነውም በሃሳብ ደረጃ መታገል ስንችል ለአገር ሰላምና ዕድገት ተመራጭ መንገድ መሆኑን ገልጸዋል።

በእናቶችና አባቶች ደምና አጥንት ክብሯን ጠብቃ የኖረችውን ኢትዮጵያ ልናሸጋግር የምንችለው ሁላችንም ድርሻ አለን ብለን ስናምን፣ ግልጽና ሃቀኛ ስንሆን ነው ብለዋል።

ታሪክ በሌሎችም መስኮች መደገም ይኖርበታል ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ ሁሉም በተሰለፈበት መስክ ጀግንነትን ለመድገም መንቀሳቀስ ይገባዋል፣ አርበኞች እንዳስተማሩት የድል ሚስጥሩ ጀግንነትና እንደ አገር አብሮ መቆምና መደጋገፍ እንደሚገባም መክረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ድሎቻችን ለኢትዮጵያ በጨለማ ውስጥ ብርሃን መፈለግን፣ በመከራ ውስጥ ተባብሮ መስራትን፣ በጭንቅ ጊዜ ተስፋ ማድረግን አስተምረውናል፤ በተለይ አሁን ለምንገኝበት ሁኔታ አስፈላጊ ስንቅ ናቸው።

የአድዋ የአርበኞች ድል መንፈስ እየታደሰ የሚቀጥልና ለዘላቂ የኢትዮጵያ ጥቅሞች ልናውላቸው ይገባል። አርበኞች የፋሽስት ጣሊያን ወረራን በመቃወም ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል የአገርን ሉዓላዊነት አስከብረዋል ከፍተኛ ክብር ይገባቸዋልም ብለዋል።

በኢትዮጵያ አስከፊ ጦርነት መካሄዱን ያስታወሱት

‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‹‹ትውልዱ ከዋልታ ረገጥ አስተሳሰብ በመላቀቅ አገሩን ማፅናት ይጠበቅበታል››

### - የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

አዲስ አበባ፡- ትውልዱ ፅንፈኝነትና አክራሪነት ራሱን በልቶ የሚያጠፋ አስተሳሰብ መሆኑን ከፋሺስታዊ አገዛዙ በመማር ከዋልታ ረገጥ አስተሳሰብ በመላቀቅ አገሩን ማፅናት ይጠበቅበታል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት 81ኛው የአርበኞች መታሰቢያ ቀንን በማስመልከት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤የፋሽስቱ አገዛዝ እንደ ወሳኝ የማሸነፊያ መሳሪያ ተማምኖ የነበረው በታሪክ “ፋሺዝም” ተብሎ የሚታወቀውን ጫፍ የረገጠ ፅንፈኝነትና አክራሪነትን ነበር። ትውልዱ ፅንፈኝነትና አክራሪነት ራሱን በልቶ የሚያጠፋ አስተሳሰብ መሆኑን ከፋሺስታዊ አገዛዙ በመማር ከዋልታ ረገጥ አስተሳሰብ በመላቀቅ አገሩን ማፅናት ይጠበቅበታል።

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ፈልጋ የሰውን አገር ወራ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

ባታውቅም ጠላቶቿ አልተኙላትም፣ አይተኙምም ያለው መግለጫው፤ በሕዝቦቿ ህብረ-ብሔራዊ አንድነትና በአልገዛም ባይነት ወኔያቸው ሉዓላዊነቷና የሕዝቦች ነፃነት

”ትውልዱ ከዋልታ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለአገር ሰላምና እድገት የሃይማኖቶች መቻቻል ከምንም በላይ አስፈላጊ መሆኑ ተገለጸ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡ ለአገራችን ሰላምና እድገት የሃይማኖቶች መቻቻል ከምንም በላይ አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነ የስነመለኮትና የስነልቦና ባለሙያው ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ ተናገሩ።

ዶክተር ወዳጄነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሙስሊምና ክርስቲያ እምነት ተከታዮች ሕጉ ከሚያዘው መቻቻል አልፈው ወንድምና እህት በመሆን ለዘመናት ተከባብረው የኖሩ ናቸው። ለአገራችን ዘላቂ ሰላምና እድገት የሃይማኖቶች መቻቻል ከምንም በላይ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

በግላቸው ከሙስሊም ኡስታዝ ጓደኞቻቸው ጋር በየበዓላቱ የመልካም ምኞት መግለጫ እንደሚለዋወጡ

«ለአገር ሰላምና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ወዳጄነህ መሃረነ
















# የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ስለሚኖራቸው ሚና ጥናት እየተደረገ እንደሆነ ተገለጸ

-ጥናቱ ሲጠናቀቅም ለአገራዊ ምክክሩ ኮሚሽን የሚላክ ይሆናል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ስለሚኖራቸው ሚና ጥናት እያደረገ እንደሆነ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አስታወቀ።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የጥናት ቡድን በማደራጀት "በአገራዊ ምክክሩ ላይ ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ምን አይነት ሚና ይኑራቸው" የሚል ጥናት እያደረገ ነው። ጥናቱ ሲጠናቀቅ ድርጅቶቹ ተለይቶ የሚታወቅ እና በጥናት ላይ የተመረኮዘ ሚና እንዲወጡ ይደረጋል።

ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የጥናቱ ውጤት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለውይይት እንደሚቀርብና ድርጅቶቹ በአገራዊ ምክክሩ አወንታዊ እና ገንቢ ሚና ይኖራቸዋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸው ፤ጥናቱ ከአንድ ወር በኋላ ተጠናቆ ለአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም እንደሚላክ ገልጸዋል።የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከባህሪያቸው በመነሳትም የሚኖራቸው ሚና የሚወሰነው በምክክር ኮሚሽኑ እንደሚሆንም ገልጸዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከባህሪያቸው ስንነሳ ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ ለመንግሥት የማይወግኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ናቸው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለየትኛውም አካል ያልወገነ ባህሪ ስላላቸው አገራዊ የምክክር መድረክ ላይ የሚኖራቸው ሚና በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል ብለዋል።


አቶ ጂማ ዲልቦ

የምክክር ኮሚሽኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች ማህበረሰቡ እንዲሁም ሲቪል ተቋማት እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው ሊወስን ይችላል ያሉት አቶ ጂማ፤ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከሚኖራቸው ሚናዎች አንዱ ማህበረሰብን ማንቃት ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ጂማ ዲልቦ አገላለጽ ፤የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 11/13 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ድርጅቶቹ ህብረተሰብን የማንቃት እና መብቱን የሚጠይቅ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።ከዚህ አኳያ ማህበረሰቡ አገራዊ ምክክሩ ላይ በንቃት እንዲሳተፍ የማድረግ ኃላፊነትም አለባቸው። ህዝብን ከማንቃት ጎን ለጎን ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚኖሩ የተለያዩ መድረኮችን በማመቻቸት፣ በቴክኒክ እና በገንዘብ በመደገፍ መድረኮቹ ውጤታማ እንዲሆኑ ሊያግዙ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በአንዳንድ አገራት ባለው ተሞክሮ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቀዳሚነት ሚና በመውሰድ አገራዊ ምክክሮችን የመሩባቸው አገራት እንዳሉ ያስታወሱት አቶ ጂማ፤ በቱኒዚያ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2015 የተደረገውን ምክክር የመሩት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።

የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎችን በመቅሰም በእኛም አገር ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው እንደሚጠበቅም ተናግረዋል።

በባለስልጣኑ አማካኝነት ከተቋቋመው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ ከኮሚሽኑ ጋር ንግግር እንደተጀመረ ጠቁመው፤ ባለስልጣኑም ይህንን ነገር በማጠናከር በቀጣይ ከኮሚሽኑ ጋር ወይይት እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትቀጥልና ለችግሮች ዘላቂ እልባት ለመስጠት አገራዊ ምክክሩን ማሳካት አለብን ያሉት አቶ ጂማ፤ የሚመለከታቸው አካላት ሲቪል ማህበረሰቡ፣የግሉ ሴክተር እና ማህበረሰቡ ምክክሩን በቀና ልብ እንዲመለከቱትና ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡት ጠይቀዋል።

# ወጣቱ ትውልድ የጥንታዊ አርበኞችን ድል በዛሬዋ ኢትዮጵያ መድገም እንደሚጠበቅበት ተገለፀ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

**አዲስ አበባ**፡ ወጣቱ ትውልድ የጥንታዊ አርበኞችን ድል በዛሬዋ ኢትዮጵያ መድገም እንደሚጠበቅበት በ81ኛው የጀግኖች አርበኞች ድል መታሰቢያ በዓል ላይ የተገኙ ወጣቶች ተናገሩ።

ኢትዮጵያ በጥንት አርበኞቿ ጠላትን ድል በማድረግ አንድነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያን ለዛሬው ትውልድ ያስረከቡበት ዋነኛ ሚስጥር በዘር፣ በሃይማኖት እንዲሁም በሌሎች ውስጣዊ ችግሮቻቸው ሳይከፋፈሉ ለአንድ አላማ በአንድነት መቆማቸው እንደሆነ ገልፀዋል።

ዛሬ ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ ባንዳዎችና ጠላቶች እንዳትደፈር ተከብራና ታፍራ እንድትኖር ወጣቱ ትውልድ ልክ እንደ አባት አርበኞች ሁሉ ሀገሩን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ሊያስረክብ ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል ወጣቱ አርበኞች ያደረጉትን ተጋድሎ በተገቢው በማወቅና በመገንዘብ ከእነሱ ጀግንነትንና ጥንካሬን በመላበስ በሚጠበቅበት ሁሉ ሊወጣ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ከአዲስ አበባ አስካውት ካውንስል የመጣው ወጣት ሙሉጌታ ታደሰ አባት አርበኞቻችን ሃይማኖትን፣ ጎሳን እንዲሁም ዘርና ቀለም ሳይለያቸው ሀገራችንን ለዛሬ ያበቁት በሰውነታቸው ብቻ በመተሳሰብ ለአንድ አላማ ለሀገራቸው መቆማቸው እንደሆነ ገልጿል።

ጠላትም ኢትዮጵያን ሊያጠፋና ሊበዘብዝ እንጂ የአንድን ብሔር ወይም የአንድን ዘር ለይቶ ለማጥቃት ባለመሆኑ የአሁኑ ወጣት ውድ የሕይወት ዋጋ ተከፍሎ የተሰጠውን አገር በአግባቡ ጠብቆና አልምቶ ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ጠቁሟል።

ሌላኛዋ የአዲስ አበባ ነዋሪ ወይዘሪት መምበረ ማርቆስ በበኩሏ አባቶቻችን በአንድነትና በፍቅር እንዲሁም በጀግንነት ሀገራችንን ለዚህ ያበቁ መሆኑን አውስታ፤ ልክ እንደ ጥንት አባቶቻችን እርስ በእርስ ባለመጠራጠር፣ የሀገርን ህልውና አሳልፎ ከመስጠት በመቆጠብ እንዲሁም ለጠላት ወራሪዎች እጅ ባለመስጠት በአንድነት መቆም ያስፈልጋል ብላለች።

በአሁኑ ወቅት ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ሆነው ሀገር በጠላት እጅ እንድትወድቅ የሚጥሩ አካላት


ፎቶ ዳኜ አበራ
መምበረ ማርቆስ


ሙሉጌታ ታደሰ

እንደሚኖሩ በመጠቀም ልክ እንደ አባቶቻችን ባንዳነት ሳይበግራቸው እራሳቸው አልፈው ሀገር እንዳቆዩት ሁሉ የዚህ ትውልድ ባለቤትም ይህን የጀግንነት ታሪክ መድገም እንዳለበት ጠቁማለች።

በተለያዩ ወቅት ኢትዮጵያ ከተለያዩ ጠላቶቿ ጋር በገጠመችው ጦርነት ሳትሸነፍ ለዛሬ መድረሷና ለሚቃጣባት የህልውና አደጋ እጅ ባለመስጠት ዛሬ ላይ የደረሰች ሀገር መሆኗን የተናገረው ሌላኛው ወጣት ግርማ ስሜ፣የቀደመውን የህዝቦቿን አንድነትና ጥንካሬ በማስቀጠል አሁን የሚታየውን የመከፋፈልና የእርስ በእርስ መጠራጠር የሚሻገር ትውልድ መገንባት ይገባል ብሏል።

ከአርበኞች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የድል መታሰቢያ በዓሉ ላይ የተገኘችው ተማሪ ናርዶስ አበራ፣ የአባት አርበኞችን በወቅቱ ያለውን የአብሮነት፣ የመቻቻልና ሀገር ፍቅር መልካም እሴቶች በተገቢው በመረዳትና በመገንዘብ የአሁኑ ትውልድ አገር ለመገንባትና ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ሊጠቀምበት እንደሚገባ ተናግራለች።

አባቶቻችን የሀገራቸውን ፍቅር በማስቀደማቸው ምክንያት የሀገራችን ሉዓላዊነት ተጠብቆ፣ ቋንቋና ባህላችን ሳይበረዝ ዛሬ ላይ ደርሷል ያለችው ወጣቷ፤አባቶቻችን ደማቅ የታሪክ አሻራ እንዳሰፈሩት ሁሉ የዚህ ትውልድ ባለድርሻ ሁሉ የሚጠበቅበትን ከማድረግ ባሻገር የሀገሩን ክብርና ዝና በሚያንቋሽሹ አካላትን መታገስ የለበትም ብላለች።

# የአሳማ መኖን ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር በመቀላቀል የምግብ ዘይት ሲያመርቱ የተገኙ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ዋሉ

አዲስ አበባ፡- የአሳማ መኖን ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር በመቀላቀል የምግብ ዘይት ሲያመርቱ የተገኙ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን አስታወቀ።

ግለሰቦቹ በደቡብ ጎንደር ዞን ወረታ ከተማ የአሳማ መኖ፣ የዘይት ተረፈ ምርትን (ፋጉሎን)፣ ሱፍን እና ሌሎች ለጊዜው ምንነታቸው ያልተለዩ በማዳበሪያ ታስረው የተቀመጡ ነገሮችን ቀላቅሎ በማፍላት እና በሰው እግር በመርገጥ ህገ-ወጥ ዘይቱን እንደሚያመርቱ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከማህበረሰቡ በደረሰው ጥቆማ መሰረት ከአማራ ጤና ቢሮ እና ከደቡብ ጎንደር ዞን መስተዳድር ጋር በመሆን ባደረገው ክትትልና ፍተሻ ነው ለምግብነት ሊውል የማይችለውን ዘይት በቁጥጥር ሥር ያዋለው።

የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ ሙሉጌታ ቆየ እንደገለጹት የምርቱ ናሙና ተወስዶ በላብራቶሪ ሲመረመር በተለያየ መለኪያ ከመውደቁ ባሻገር ከፍተኛ የአሲድ ክምችት እንደተገኘበት አስታውቀዋል።

አክለውም ምርቱ በምንም መመዘኛ ለምግብነት ሊውል የማይችል እና ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ እንደሆነ ገልፀው፤ ምንም አይነት የብቃት ማረጋገጫ ያልተሰጠውና ለህብረተሰቡ የሚከፋፈለውም ሳይታሸግና የምርት መለያ ሳይለጠፍበት ከበርሜል በመቅዳት መሆኑን አብራርተዋል።

በሀገሪቱ የተከሰተውን የምግብ ምርቶች ዋጋ መናርን ተከትሎ ጥራትና ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ምርቶች የጤና ጉዳት እንዳያደርሱ ህብረተሰቡ በየአካባቢውና በግብይት ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

በምግብና መድኃኒት ምርት፣ ንግድና ዝውውር ላይ አጠራጣሪ ነገሮች ሲያጋጥሙ ህብረተሰቡ በአካባቢው ላሉ የህግ አስከባሪ አካላት ወይም በነፃ የስልክ መስመር 8482 በመደወል ጥቆማ መስጠት እንደሚችል ከባለስልጣኑ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ዜና

# ክልሉ በድርቁ ምክንያት ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ እንዳልቻለ ገለጸ

• ድርቁ ባስከተለው ጫና ከ2015 በጀቱ ላይ ተቀናሽ የሚሆን 500 ሚሊዮን ብር ተበድሯል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡ በክልሉ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት እስካሁን መሰብሰብ ከነበረበት ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ እንዳልቻለ የሱማሌ ክልል የፋይናንስ ቢሮ አስታወቀ። ድርቁ ባስከተለው ጫናም ከ2015 ከሚመደብለት በጀት ተቀናሽ የሚሆን 500 ሚሊዮን ብር ተበድሯል።

የሶማሌ ክልል የፋይናንስ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሙሄዲን አብዲ ፋራህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እስካሁን ክልሉ መሰብሰብ ከነበረበት ገቢ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ አልቻለም።ምክንያቱም ድርቁ ባስከተለው ጉዳት ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የቁም እንስሳት ሞተዋል። እንስሳቶች በመሞታቸውና በመጎዳታቸው ከእንስሳቱ ሽያጭ ይገኝ የነበረው ገቢ ሳይገኝ ቀርቷል።

በክልሉ በ40 ዓመታት ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ አስከፊ ድርቅ ተከስቷል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤የድርቁ ጉዳት እንዲባባስ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተከሰተው ጦርነት መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ ዳር ድንበር ሲጠብቅ የቆየው የምስራቅ እዝ ወደ ጦርነቱ በተንቀሳቀሰበት ወቅት ክልሉ የአገሪቱን ድንበር ከጸረ ሰላም ኃይሎች ለመጠበቅ ተልዕኮ በመውሰዱ


ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ
**ሙሄዲን አብዲ ፋራህ**

የክልሉን ጠቅላላ መጠባበቂያ በጀት ለዳር ድንበር መጠበቂያ በማዋሉ አውስተው፤ክልሉ ከሁለት ሺ 500 በላይ ኪሎ ሜትር የሚሸፍነውን ዳር ድንበር በፖሊስ፣ በልዩ ኃይል፣ በሚሊሻ ለመጠበቅ የሚያስችል ግብዓት ለማሟላት በጀቱን በመጠቀሙ ድርቁ ላስከተለው ጉዳት ድጋፍ ማድረግ የሚችልበት አቅም ማጣቱን ተናግረዋል።

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በክልሉ የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም ሲባል ለአዳዲስ የውሃ፣ የትምህርት፣ የጤናና መሰል ፕሮጀክቶች ለመገንባት የተበጀተው አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ድርቁ ላስከተለው ችግር እንዲውል ተደርጓል።

በግንቦት ወር ዝናብ ካልዘነበ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ሁሉ የመቋረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ሙሄዲን፤ ድርቁ ክልሉን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተነ በመሆኑ ደመወዝና የሥራ ማስኬጃ ብቻ እንዲከፍል ሁኔታው ያስገድዳል ብለዋል።

በክልሉ ድርቁ ያስከተለው ችግር በመባባሱ የፌዴራል መንግሥት ለክልሉ በ2015 ከሚበጅተው በጀት ላይ ተቀናሽ የሚሆን 500 ሚሊዮን ብር በመበደር ለድጋፍ እያዋለ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በድርቁ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የቁም እንስሳት መሞታቸውን አመልክተው፤ እስካሁን ክልሉ መሰብሰብ ከነበረበት ገቢ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ አልቻለም። ይህም በፋይናንስ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና ማሳደሩን አቶ ሙሄዲን ገልጸዋል።

እንደ ሽበሌና ገናሌ ያሉ የተፋሰስ ወንዞችን በመጠቀም ህብረተሰቡ እንዴት ምርት ማምረት እንዳለበት በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸው፤ድርቁ ያስከተለው ጉዳት በክልሉ አቅም የሚቀረፍ ባለመሆኑ እስካሁን እየተደረገ ያለው ድጋፍም ከተከሰተው ጉዳት አንጻር የማይጣጣም በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ‹‹ትውልዱ በብሔርና በሃይማኖት ሰበብ ግጭት ውስጥ ከሚገባ ይልቅ ኢትዮጵያን በአንድነት ሲያስቀጥል ይገባል››

## አባትና እናት አርበኞች

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡-አበባ፡-የአሁኑ ትውልዱ በብሔርና በሃይማኖት ሰበብ ግጭት ውስጥ ከሚገባ ይልቅ በአባቶቹ ተጋድሎ ያገኛትን አገር በአንድነትና በትብብር ሊያስቀጥል ይገባል ሲሉ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አባትና እናት አርበኞች ገለጹ።

በ81ኛው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች የድል መታሰቢያ በዓል ላይ የተገኙት ልጅ ከተማ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጥንት አርበኞች በዱር በገደሉ ታግለው ጠላትን አሳፍረው ነጻ አገር ለአሁኑ ትውልድ አስረክበዋል። ከአባቶች የወረስነው ለአገር መሞትን፣ መተባበርንና አንድነትን ነው። ኢትዮጵያ የቆየችው ከጥንት ጀምሮ ጀግኖች አባቶች በከፈሉት መስዋዕትነት ነው።

በአባቶች ተጋድሎ ያገኛትን ነጻ አገር የአሁኑ ትውልድ ከተራ የብሄርና የሃይማኖት ግጭት ወጥቶ የአገሩን ክብርና ሰላም በዘላቂነት ማስቀጠል አለበት ብለዋል።

እንደ ልጅ ከተማ ገለጻ፤ እኔ ከአባቶቼ የወረስኩት ኢትዮጵያዊነትን ነው። የአሁኑ ትውልድ ትክክለኛውን የጥንት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞችን የጀግንነት ገድል በትክክል ቀርጾ በማስተማርና በመማር በዓሉንም በትክክል መዘከር ይገባል። ምክንያቱም ታሪኩን በትክክል የሚያውቅ ትውልድ በብሔርና በሃይማኖት ሰበብ ግጭት ውስጥ እየገባ አገርን አደጋ ላይ አይጥልም።

ትውልዱ መጀመሪያ መማር ያለበት አገርን ፍቅርና አንድነት መሆኑን አመልክተው፤የኢትዮጵያ አርበኞች፤ ለአገር ነጻነት፣ አንድነትና ክብር ሲሉ ከሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫዎች በመጉረፍ ጠላትን ድባቅ በመምታት ድል አድርገው አልበገር ባይነትን ያስመሰከሩበት መሆኑን በዓሉን ለመታደም የአባቷን የአርበኝነት ታሪክ ወርሳ ልጇን አዝላ በድል መታሰቢያ በዓሉ ላይ የተገኘቸው ልጅ ሳባ በላይ ተናግራለች።

የአሁኑ ትውልድ በብሔር፣ በሃይማኖት ሽፋን ሲጋጭ በአባቶቹ ታሪክ እየቀለደ መሆኑን መገንዘብ አለበት ያለችው ልጅ ሳባ፤ በሕይወት ካሉት ከጥንታዊት ጀግኖች አርበኞች ማህበር ታሪኩ ሳይበረዝና ሳይከለስ ትክክለኛ ታሪኩን መማር አለበት። ‹‹እኔ ከአባቴ እውነተኛ የአገር ፍቅርና ታሪክ ወርሻለሁ፣ ለልጅ ልጆቼም አወርሳለው›› ስትል ገልጻለች።


ፎቶ ዳኜ አበራ
**አባት አርበኛ ዳኛቸው ንጉሴ**


**እናት አርበኛ ሽታየ ታደሰ**

አባቶቻችን ለአገር ሲሉ ተሰውተው ነጻ አገር አስረክበውናል፤ የአሁኑ ትውልድ የሚጠላው ምን ለማግኘት ነው? ጥንት ጠላቶቻችን በሚሸርቡት ሴራ በመጠለፍ አገርን አደጋ ላይ መጣል ከባድ ታሪካዊ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብላለች።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር የምክር ቤት አባል አባት አርበኛ ዳኛቸው ንጉሴ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ጥንት እናት አባቶቻችን በጦር በጎራዴ በኋላ ቀር መሳሪያዎች ስንቅም ትጥቅም በሌለበት ዘመን ዘመናዊ መሳሪያ ታጥቆ የመጣውን ወራሪ በጀግንነት ተፋልመው አሳፍረው በመመለስ ነጻ አገር ለአሁኑ ትውልድ አስረክበዋል። ከጥንት ተጋድሎ ከሞት የተረፉትን አርበኛ አባቶችና እናቶችን አርዓያ በማድረግ የአሁኑ ትውድ ኢትዮጵያን በሚመጥን መልኩ አንድነትን ማስቀጠል እንዳለበት ጠቅሰዋል።

ድል ተደርገው አፍረው የተመለሱት ጠላቶች አሁንም የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነት ስለማይፈልጉ በብሔር፣ በሃይማኖት ሽፋን ግጭት ለመፍጠር እየሰሩ ነው ያሉት አባት አርበኛው፤ ወጣቱ ሴራውን በመገንዘብ ከአላስፈላጊ ግጭት መውጣት አለበት። በአሉቧልታ ወሬ ሳንበረዝ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ባንዳ ሆኖ የሚመጣውን ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋልም ብለዋል ።

ኢትዮጵያ መኖሪያችን፣ መቀበሪያችን እናት አገር ስለሆነች፤ ወጣቱ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት የተጀመሩ ልማቶችን አጠናክሮ ማስቀጠል አለበት።የአገሩን ዳር ድንበር መጠበቅ እንዳለበት ተናግረዋል።

እናት አርበኛ ሽታየ ታደሰ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ትውልዱ ከመጋጨት ወጥቶ ጥንት አባቶቹ በመከባበር በአንድነት ያቆይዋትን አገር በፍቅርና በሰላም ማስቀጠል አለበት። ኢትዮጵያ የሁሉም ናት፣ ደማችን፣ መልካችን ናት። ማንም ሊለያየን አይችልም።

ትውልዱ ከብሔርና ከሃይማኖት ግጭት ወጥቶ በፍቅርና በአንድነት አገሩን ሊያስቀጥል እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሃይማኖትና ብሔር የአንድነት እንጂ የልዩነትና የግጭት መንስኤ ባለመሆኑ በሃይማኖትና በብሔር ስም ግጭት ውስጥ የሚገቡ ወጣቶች ሰከን ብለው ሊያስቡና በአገራቸው ላይ የተሸረበውን ሴራ ሊያከሽፉ ይገባል ብለዋል።


ፎቶ፡- ናሆም አየለ
**አቶ መላኩ አለበል**

# የ‘ኢትዮጵያ ታምርት‘ ንቅናቄ ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደሥራ ለማስገባት እንደሚረዳ ተገለፀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የ‘ኢትዮጵያ ታምርት’ ንቅናቄ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት እና ከአቅም በታች የሚያመርቱትን ወደ ማምረት አቅማቸው ለመመለስ የሚረዳ እንደሆነ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለፀ።በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ካቆሙ 446 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 118 ያህሉ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ሥራ ተመልሰዋል ተብሏል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በትላንትናው ዕለት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር ዕቅድ አፈፃፀምን ሲያቀርቡ እንደገለፁት፤ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ የሚመልስና በማምረት አቅማቸው ልክ የማያመርቱትን የግብዓትና የመሳሰሉ ችግሮቻቸውን በመፍታት በሙሉ አቅማቸው እንዲያመረቱ የሚያስችል ሥራ የሚሠራበት ነው።

ኢንዱስትሪዎችን መሠረት አድርጎ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ኢንዱስትሪዎች ላይ ያሉ ችግሮች በጥልቀት ተመርምረው መታወቃቸውን ገልፀው፤ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ከተቀመጡ የመፍትሄ አቅጣጫዎች አንዱ የ‘ኢትዮጵያ ታምርት’ ንቅናቄ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢንዱስትሪዎች ተፈጥሯዊ በሆነ ባህሪያቸው በውድድር ምክንያት የሚከስሙ ሊኖሩ እንደሚችሉ የጠቀሱት አቶ መላኩ፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ችግርና መሠረተ ልማት ዝርጋታ መጓተት ምክንያት የቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ የመመለስ እንቅስቃሴ ይካሄዳል ።ከዚህ ቀደም በተሠሩ ሥራዎችም ሥራ ካቆሙት 446 ኢንዱስትሪዎች 118 ያህሉ ወደ መደበኛ ሥራቸው ተመልሰዋል ብለዋል።

በተለያየ መልኩ ሥራ አቁመው ከሚገኙት ኢንዱስትሪዎች በተጨማሪ በጦርነት ምክንያት ሥራ ያቆሙና ጉዳት የደረሰባቸው በርካታ ኢንዱስትሪዎች መኖራቸውንም ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለፃ፤ በጦርነቱ ምክንያት ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍ ረዘም ላሉ ጊዜያት በኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጊዜያዊ ቢሮ በመክፈት ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። በጦርነት ምክንያት ሥራ ያቆሙ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን እንዴት እንደሚደግፉና ኢንዱስትሪዎቹ ወደ ሥራ እንዲገቡ እንደሚያደርጉ የክልሉና የከተማ አስተዳደሩ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

በሌላ በኩል የውጭ ምንዛሪ፣ የጥሬ ዕቃ፣ የፋይናንስ፣ የመለዋወጫ ዕቃ እና ሌሎች ችግሮች ያሉባቸው ኢንዱስትሪዎችን በተመለከተ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሙሉ ጥናት አጥንቶ ለሚመለከታቸው አካላት መፍትሄ እንዲሰጣቸው ቀርቧል ብለዋል። ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለመፍታት በሂደት ላይ እንደሚገኙም ሚኒስትሩ ገልፀዋል።

ዜና

# ለጎረቤት ሀገራት ከቀረበ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ 37 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኘ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለጎረቤት ሀገራት ከቀረበ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ 37 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

በቀጣይም ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት የምታቀርበውን የኤሌክትሪክ ኃይል በማሳደግ ገቢውን እንዲጨምር እየተሰራ መሆኑ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ይህን ያለው በደቡብ ሱዳን የኢነርጂና ግድብ ሚኒስትር ፒተር ማርሴሎ ናስር የተመራ ልዑክ የኢትዮጵያን "ብሔራዊ ኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠሪያ ማዕከል" በጎበኘበት ወቅት ነው።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ፕላኒንግ ሥራ አስፈፃሚ አቶ አንዱለም ሲያ፤ ኢትዮጵያ ያላትን የተሻለ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ለደቡብ ሱዳን ልዑኩ ማሳየት መቻሏን ገልጸዋል።

ጉብኝቱም ሁለቱ ሀገራት በኃይል መሰረተ ልማት በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ያለመ እንደሆነ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያም በመጀመሪያ ምዕራፍ እስከ ሶስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለደቡብ ሱዳን 100 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ ያቀደች ሲሆን በሂደት ደግሞ ከ400 ሜጋ ዋት በላይ ኃይል ለማቅረብ ይሰራል ብለዋል።

ኢትዮጵያ 254 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለሱዳንና ጂቡቲ እያቀረበች መሆኗንም ጠቅሰዋል።

ለጎረቤት ሀገራት ከሚቀርብ ኃይል ሽያጭ በዓመት እስከ 50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የደቡብ ሱዳን የኢነርጂና ግድብ ሚኒስትር ፒተር ማርሴሎ አገራቸው ከኢትዮጵያ የምታገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል ለኢኮኖሚ እድገቷ የሚያግዝ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህን ታሳቢ በማድረግም ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችላትን ስምምነት እንዲደረስ ልዑካቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የሥራ ጉብኝት እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በደቡብ ሱዳን የኢፌዴሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ነቢል መሐዲ፤ ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ የኃይል አቅርቦት ግዥ ስምምነት እንድትወስድ የተለያዩ ሥራዎች ሲካሄዱ መቆየቱን ገልጸዋል።

የሁለቱን ሀገራት ህዝቦች ምጣኔ ሐብታዊ ተጠቃሚነት ለማሳዳግም በኃይል፣ በመንገድና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች ለማስተሳሰር በቅርበት እየተሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ሁለቱ ሀገራት ያካሄዱት የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ረቂቅ ሰነድ ላይ ምክክር በማካሄድ የመግባቢያ ስምምነት ይፈራረማል ተብሎ ይጠበቃል።

በቀጣይም ኢትዮጵያ ለታንዛንያ፣ ለርዋንዳና ብሩንዲ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን በኃይል መሰረተ ልማት ለማስተሳሰር በትኩረት እየሰራች እንደሚገኝ መገለፁን የኢዜአ ዘገባ ያመለክታል።

# ለአገር ሰላምና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጠቁመው፣ የሙስሊምና የክርስቲያ እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን ወንድማማችነት የማይፈልጉ እና የሚያስቆጣቸው ኃይሎች የሃይማኖት ችግርን ለኩሰን አገሪቱን ለችግር እንዳርጋለን ብለው በማሰብ ችግር ለመፍጠር ቢሞክሩም አይሳካላቸውም ብለዋል።

ሙስሊም እና ክርስቲያኑ ጠብቀነው የኖርነውን ወንድማማችነታችንን፣ አብሮነታችንን ፣መዋደዳችንንና መተሳሰባችንን አሁንም ጠብቀነው መዝለቃችን ለአገራችን ዘላቂ ሰላምና እድገት ወሳኝ ነው ብለዋል።

ዶክተር ወዳጄነህ እንደሚሉት ህዝቡ አይቀበላቸውም እንጂ እነዚህ ኃይሎች የሚያስቡት አንዱ አንዱን እየጎዳ በአገራችን የማይበርድ የሃይማኖት ችግር እንዲፈጠር ነበር። በአገራችን የሚፈጠሩ ሃይማኖት ነክ ችግሮች መነሻቸው ከውስጥ አይደለም።

ችግሩንየሚፈጥሩትየሙስሊምእናየክርስቲያኑን ወንድማማችነትን የማይፈልጉና የሚያስቆጣቸው ኃይሎች ናቸው ያሉት ዶክተር ወዳጄነህ፤ አሁንም ጠላት እንደማይሳካለት እና በአገራችን ሃይማኖቶች ተከባብረው በወንድማማችነት እየኖሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

የተፈጠረው ችግር ከሙስሊሙ ወይም ከክርስቲያኑ በኩል የመጣ ሳይሆን ሆን ተብሎ የተፈጠረ ከውጭ ወገን አገራችንን ለመጉዳት ታስቦ የመጣ በመሆኑ ኡስታዞች፣የኦርቶዶክስ መምህራን፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አባቶችና የወንጌላውያን አብያተክርስቲያን ሰባኪዎች ለዘመናት የቆየውን የሃይማኖቶች መከባበርና ወንድማማችነት እንዳይቀዘቅዝ እና ጠላትም ጣልቃ እንዳይገባ መስራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል።

በታላቁ የረመዳን ጾም አፍጥር እየተጋበዝን በጋራ ስናፈጥር ነበር ያሉት ዶክተር ወዳጄነህ፤ ይሄንን ወንድማማችነት አውጥቶ ማሳየት ያስፈልጋል ብለዋል። በህዝበ ክርስቲያኑ እና ሙስሊሙ መካከል ምንም ችግር እንደሌለ በአደባባይ ማሳየቱ ወንድማማችነቱ እና እህትማማችነቱን አሁንም እንደቀጠለ ማሳያ እንደሆነም ገልጸዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ እና ክርስቲያኑ ለዘመናት ተከባብሮ በወንድማማችነት እና በእህትማማችነት የኖረ እንደመሆኑ አሁንም አገራችንን ለመበጥበጥ እኩይ አላማ ይዘው ለሚንቀሳቀሱ የውጭ ኃይሎች መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።«የሃይማኖት ችግርን ለኩሰን አገሪቱን ለችግር እንዳርጋለን» ብለው የሚያምኑ ጠላቶቻችን አሳፍሮ መመለስና ለእኩይ አላማቸው ተገዥ አለመሆን እንደሚገባም አስታውቀዋል።

# "ትውልዱ ከዋልታ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተጠብቆ ይቀጥላል ብሏል።

ዛሬም አገራችን ከቅርብና ከሩቅ ታሪካዊ ጠላቶቿ በሚሰነዘርባት ሁለንተናዊ ጥቃት ሳትንበረከክ ልጆቿ ከአባቶቻችን በወረሱት የአገር ፍቅር ለሕዝቦች ክብርና ለአገር አንድነት ዘብ መቆማቸውን መግለጫው አመልክቶ፤ መጪው ትውልድም ለጋራ አገሩና ለክብሩ በአንድነት በመቆም ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ እንደሚያሸጋግራት ጥርጥር የለውም ሲል ገልጿል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ በርካታ ጦርነቶችን አካሂዳለች። ጠላቶቿ የተኙላት ጊዜ የለም። ኢትዮጵያ በታሪኳ ጦርነት ፈልጋ እና ተመኝታ፣ የሌላውን ሉዓላዊነት ጥሳ ወረራ ፈፅማ አታውቅም ያለው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ፤ ሁሌም የራሷ በሆነው ሃብት ወይም ሌላ ጉዳይ በጠላቶቿ ትጠቃለች። ሆኖም ግን ሁሉንም ጦርነቶች በአሸናፊነት አጠናቃለች። ጦርነቶቹን ያሸነፈቻቸው በጠላቶቿ ድክመት ወይም በታጠቀቻቸው ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ብልጫ አለመሆኑንም መግለጫው አውስቷል።

ሁሌም ጠላት ሲመጣ በሚሰባሰቡትና ጠላትን በአንድነት በሚመክቱት ጀግኖች ልጆቿ ነው። ሁሌም ኢትዮጵያ በጠላቶቿ ስትነካ ትዕግስት የሌላቸው ውድ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት በደምና በአጥንታቸው የአገራቸውን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ሳይደፈር አስከብረው አቆይተዋቸውንም መግለጫው አብራርቷል።

በታሪክ ሁልጊዜ ከሚታወሱት የጀግንነት ታሪካችን አንዱ ከስምንት አስርት-ዓመታት በፊት ለአገር ክብርና ለሕዝቦች ነፃነት የአባት አርበኞች የፈፀሙት ገድል ነው። በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል የተደረገው የአድዋ ጦርነትና ጦርነቱ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መፈፀሙ በወራሪዎች ዘንድ ከፍተኛ የውርደት ስሜትና ፀፀት አስከትሏል። ሽንፈቱ በወቅቱ የበቀል ስሜትን ቀስቅሷል። ከስሜትም አልፎ የአገዛዝና የአስተሳሰብ ለውጥን አስከትሏል ብሏል መግለጫው።

ከእነዚህም ለውጦች መካከል አንዱ የፋሽስታዊ አስተሳሰብ መወለድና የመሪው ቤኒቶ ሙሶሎኒ የመንግሥት ስልጣን መቆናጠጥ ነበር። ይህ ፋሽስታዊ ብሔርተኝነትና መሪው እንደ ግብ ከያዘው አንዱ እና ዋነኛው ኢትዮጵያን ዳግም በመውረር ከሽንፈቱ ድባቴ በመላቀቅ የጣሊያንን ታላቅነት መመለስ የሚል ነበር። በዚህ መሰረት ከ40 ዓመት የአድዋ ድል በኋላ ፋሽስታዊ አገዛዙ እ.አ.አ በጥቅምት 1935 ዓ.ም ኢትዮጵያን መውረሩን መግለጫው አውስቶ፤በወቅቱ የጠላት ጦር በያዘው የጦር መሳሪያና በሰለጠነ የወታደር የበላይነት ምክንያት ለጊዜውም ቢሆን የወገን ጦርን ለመበተን ቢችልም ለባርነትና ለጠላት እጅ መስጠት የማያውቁ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን በማደራጀት በአዲስ መልክ በጠላት ላይ መነሳታቸውን አስገንዝቧል።

አርበኞቹ በመላ ኢትዮጵያ በብሔርና በቋንቋ ሳይለያዩ በሁሉም አካባቢዎች በመደራጀትና በመንቀሳቀስ ጠላትን እንቅልፍ አሳጡት። ለአምስት ተከታታይ ዓመታት ጠላትን እረፍት በመንሳት እ.አ.አ ግንቦት 5 ቀን 1941 አርበኞቹ የነፃነት ታጋዮች በጠላት ላይ ድል መቀናጀታቸውን መግለጫው አብራርቷል።

ዕለቱም እስከ ዛሬ ድረስ የአርበኞች የድል ቀን በመባል ይከበራል። ጀግኖች አርበኞችም ለአገራቸው ክብርና ለሕዝቦቿ ነፃነት ላደረጉት ተጋድሎ በየዓመቱ ሚያዝያ 27 ቀን ይወደሳሉ፣ ይታወሳሉ፤ ለዘለዓለም በትውልድ ሲወደሱም እንደሚኖሩ የጠቆመው መግለጫው፤የዘንድሮውን 81ኛው ዓመት የአርበኞች መታሰቢያ ቀን ስናከብር የድሉን ትሩፋቶች በማጉላትና ለትውልድ በማስተላለፍ መሆን ይኖርበታል ብሏል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመግለጫው።

# ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ፤ ጠላት ድንበር ጥሶ ወረራ ፈጽሞ ሳይሆን የኢትዮጵያ ልጆች እርስ በእርሳቸው ተዋግተዋል፣ ተገዳድለዋል፣ በርካቶች ተፈናቅለዋል ሲሉም አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፤ በበኩላቸው ኢትዮጵያውያን አንድ ስለሆንን የሚቀኑ፣ ሰላምና አንድነትን ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ፣ እንደ ቆንጆ አበባ ሊቀጥፉን የሚያስቡ ጠላቶች አሉ ብለዋል። ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ ሰላምን ለማስፈን ዘብ ሊቆም እንደሚገባውም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያን ለማቆየት አርበኞች ከጠላት ጋር ተናንቀው የከፈሉትን የሕይወት መስዋዕትነት ማሰብ እንደሚገባም አመልክተዋል። አሁን ከጣሊያኖች ጋር ያለው ግንኙነት በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲና በሁለገብ ትብብር እየተሳሰረ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በኢንዱስትሪ፣ በእርሻና በኢኮኖሚ ወደ ከፍታ ለመሻገር የሚደረገውን ጥረት ለማሰናከል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ይህንን ለማክሸፍ በጋራ መቆም እንደሚያስፈልግ ልጅ ዳንኤል ጆቴ ተናግረዋል።

የአገር መከላከያ ሰራዊት የኢንዶክትሪኔሽን ዋና ኃላፊ ሜጀር ጀነራል እንዳልካቸው ወልደኪዳን፤ ሰራዊቱ ከአባቶቹ የተቀበላቸውን የአይበገሬነት እሴት ተላብሶ በአገር ላይ የተጋረጡ የጦርነት አደጋዎችን በማምከን የጠላቶችን አንገት በማስደፋት ጀግንነቱና አይበገሬነቱን ማስመስከሩን አስታውሰዋል።

«ሰራዊቱ ሕዝብና መንግሥት የሰጡትን ኃላፊነት ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የተሻለ ቁመና ላይ ይገኛል፤ የአገር መከላከያ ሰራዊት የአገር ብዝሃነት መገለጫ፣ የአገር ብዝሃነት ማሳያ ተቋም ነው» ብለዋል።

የአገርና የሕዝብን ሰላም የማይፈልጉ ኃይሎች ሴራ መኖሩን በመገንዘብ መከላከያ ሰራዊት ከሕዝብና ከመንግሥት ጋር በመሆን በድል እየተወጣ ይገኛል ያሉት ሜጀር ጀነራሉ፤ በዘመኑ እንደ ጥንት አባቶቻችን የሕይወት መስዋዕትነት ዋጋ ከፍለን የታፈረችና የተከበረች ኢትዮጵያን ለቀጣይ ትውልድ እናስረክባለን ሲሉ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሃይማኖታዊ አክራሪነትና ጽንፈኝነትን በሃይማኖታዊ አስተምህሮ እንከላከለው

ከኢትዮጵያ በርካታ መገለጫዎች መካከል የእምነት ተቋማትና ተከታዮቻቸው ለዘመናት ተቻችሎ የመኖር እሴት ነው። ይህ መቻቻል በተለይ በእስልምና እና ክርስትና እምነት መካከል በግልጽ የሚታይ ነው። እምነቶቹና ተከታዮቻቸው አያሌ ዘመናትን አብረው ኖረዋል፤ አብሮነታቸው በብዙ መልኩ ሲገለጽም ይታያል። የእምነት ተቋማቱ በአንዳንድ አካባቢዎች ጎን ለጎን የተመሰረቱና አብረውም በርካታ ዘመናትን ያሳለፉ መሆናቸውን ለተመለከተ ከእዚህ በላይ መቻቻል የት ሊገኝ ይችላል ያሰኛል፡፡

የአንዱ እምነት ተከታይ ለአንዱ ቤተ እምነት አጥር ያስገነባል፤ መጋረጃና ሌሎች የቤተ እምነቶቹን መገልገያ የሚለግስበት ሁኔታም ይታያል፤ በዓላትን አብረው እያከበሩ፣ ደስታና መከራንውንም አብረው ሲያሳልፉ ለተመለከታቸውም የአማኙም፣ የእምነት ተቋማቱም መቻቻልና አብሮነት በእጅጉ የነገሰባቸው መሆናቸውን ማንም ባለንጹህ ህሊና ለመረዳት አይቸገርም።

ከትናንት እስከ ዛሬ ለአገር ሰላም ለማምጣት፣ የተጣለን ለማስታረቅ የእምነት ተቋማት አባቶች አብረው እየሰሩ ናቸው። ባለፉት ጥቂት አመታት ብቻ አገራችንን ሰላም የነሷት የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን በሚጭሩት እሳት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ሽቅብ ቁልቁል ደፋ ቀና ይሉ ከነበሩት መካከል የሃይማኖት አባቶች ይጠቀሳሉ። ይህ የእምነት ተቋማቱና ተከታዮቻቸው መቻቻልና ትስስር እያደር እየጠነከረ የሚሄድ እንጂ መቼም ቢሆን በቀላሉ ሊበጠስ አይችልም፡፡

ይህን ያልተረዱ የኢትዮጵያ ጠላቶች በዚያም በዚያም ቢሉት አልሳካ ቢላቸው የእምነት ተቋማቱን አንድነት ለመፈረካከስ፣ ትስስራቸውን ለማስለልና ለመበጠስ ዛሬም እየሞከሩ ናቸው። ይህ ግን የእምነት ተቋማቱና ምእመናኖቻቸው የጠላቶቻቸውን ሴራ ለማክሸፍ ይበልጥ አብረው እንዲሰለፉ አረጋቸው እንጂ እንዲፈረካከሱ አላረጋቸውም። የኢትዮጵያ መንግስትም ይህ እሴት ይበልጥ እንዲጠናከር ባለው ጽኑ እምነት የእምነት ተቋማቱን ጥያቄዎች በመመለስ፣ የሰላምና የልማት ሀይል ሆነው አብረውት እንዲሰሩ በማድረግ ላይ ይገኛል። የእምነት ተቋማቱም ጥያቄዎቻቸው በሀይል ለማስመለስ የሚሞክሩበት ወቅት ላይ አይደሉም። አብረው የሚሰሩበት መድረክም ያላቸው እንደመሆናቸው እርስ በእርስ የሚያጋጫቸው ምንም አይነት ሁኔታ የለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን የአገር ውስጥ እና የውጭ ጠላቶች በእዚህም በዚያም ብለው ሲከስሩ አንድ ቀዳዳ ፈጥረው ለማለፍ አስበዋል፤ እንደለመዱት ግርግርና ሁከት በመፍጠር በሰው ደምና ሀብት ኪሳራ ላይ እየተረማመዱ አገሪቱን ሰላም ለማሳጣት ከንቱ ሴራቸውን እየሸረቡም ለመተግበር እየሞከሩ ናቸው። ለዚህም ጥቂት የሃይማኖት አክራሪዎችን በማሰለፍ የእኩይ አላማቸው ተባባሪ በማድረግ በእምነት ተቋማቱ መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ሰርተዋል። እየሰሩም ናቸው። በእዚህም ዘመናትን የተሻገረውን የእምነት ተቋማት አንድነትና መቻቻል በመናድ እርስ በእርስ እንዲባሉ በማድረግ በጦር ሜዳ ያጡትን ድል በእዚህ ለማካካስ እየሞከሩ ናቸው።

ለእዚህ ደግሞ የሃይማኖት ጽንፈኞችንና አክራሪዎች መሳሪያ ለማድረግ በእጅጉ እየሰሩ ናቸው። በቅርቡ በጎንደር ሁከትና ግርግር እንዲፈጠርና የዜጎች ሕይወት እንዲጠፋና ጉዳት እንዲደርስ፣ ሀብትና ንብረት እንዲወድም ያደረጉትም በእዚሁ በጽንፈኝነትና አክራሪነት በሽታ በለከፏቸው አማኝ ነን በሚሉ የአገሪቱ ልጆች ነው። ችግሩንም በመላው ኢትዮጵያ ለማስፋት ተሞክሯል። የጎንደሩን ጥፋት በጥፋት ለመመለስ በመሞከር በወራቤ መሰል ጥፋት ተፈጸመ። በአዲስ አበባም በኢድ እለት በንብረትና በሰው ላይ ጉዳት ደርሷል። ይሄም መላውን ኢትዮጵያውያንንና መንግስትንም በእጅጉ አሳዝኗል።

ድርጊቱም የሃይማኖት አክራሪነትና ጽንፈኝነትን መሰረት ባደረገ መልኩ የተፈጸመ ነው። የሃይማኖት ተቋማት፣ የፌዴራሉ መንግስትና የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደሮች ድርጊቱን በጽኑ ተቃውመውታል። በዚህም እንዲህ አይነት ድርጊቶች የእምነት ተቋማትና ተከታዮቻቸውን አንድነት እንደማይሸረሽር የኢትዮጵያ ጠላቶች እንዳቀዱት እርስ በእርስ እንደማይጫረሱም አረጋግጠዋል። በጎንደርም በአዲስ አበባም ከድርጊቱ ጋር በተያያዘ የተጠረጠሩ ሰዎችም በቁጥጥር ስር እየዋሉ ናቸው፡፡

ድርጊቱ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሃይማኖት አክራሪነትና ጽንፈኝነትን በእምነት ተቋማት ውስጥ በመዝራት ሽብር እንዲፈጥሩ በማድረግ በጦር ሜዳ፣ በዲፕሎማሲና በተለያዩ መድረኮች ያጡትን ድል የሚያገኙ መስሏቸው የደገሱት ጥፋት ነው። የሆነውም ዜጎችን የጎዳ ቢሆንም፣ ለአገራችን ጠላቶች ግን እቅዳቸው ሳይሳካ የመከነበት ነው። ሆኖም አንዳንድ አካላት በእምነት ተቋማት መካከል ችግር ያለ እንዲመስላቸው አላረገም ተብሎም አይወሰድም፡፡

ከዚህ አኳያ ዜጎች በእነዚህ አክራሪና ጽንፈኛ ሀይሎች ወጥመድ ውስጥ እንዳይወድቁ ማድረግ ተገቢ ነው። አንዳንድ ምእመናን በጥቅማጥቅም ተደልለው እና ጽንፈኞች ከንቱ ስብከት ሰክረው በእዚህ የጥፋት ተግባር ተሰልፈው ሊሆን ስለሚችልም፤ ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ፤ ፍቅር፣ ወንድማማችነት፣ ሰላም፣ አንድነት፣... በሚሰብኩ የእምነት ተቋማት ውስጥ ሆነው ሊፈጽሟቸው ከተዘጋጁ ቸው ተግባራት እንዲቆጠቡ ማድረግ ያስፈልጋል። የሃይማኖት አክራሪነት በእምነት ተቋማት እንዳይሰርጽ ምዕመኑን በትክክለኛው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ በመቅረጽ መከላከል ተገቢ ነው፡፡

እያንዳንዱ እምነት ተቋም፣ የእምነት አባትና ምእመን ትክክለኛውን የሃይማኖት አስተምህሮ መሰረት በማድረግ አክራሪነትንና ጽንፈኝነትን መዋጋት ሲጀምር ደግሞ መንግስት አክራሪነትና ጽንፈኝነትን ለመዋጋት ከሚያከናውነው ተግባር በእጅጉ የሚያግዝ ይሆናል። ምክንያቱም የእምነቱ ተከታዮች በአክራሪዎችና ጽንፈኞች ወጥመድ ውስጥ እንዳይገቡ ማድረግ የሚቻለው ምእመናን በሃይማኖቱ አስተምህሮ መሰረት እምነታቸውን እንዲያራምዱ ማደረግ ሲቻል ነው። በመሆኑም ሃይማኖታዊ አክራሪነትን በሃይማኖታዊ አስተምህሮ በመከላከል፤ እንዲሁም አክራሪነትና ጽንፈኝነትን በጽኑ በመዋጋት የአገራችን ጠላቶች መፈናፈኛ ቀዳዳ እንዳያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ይብዙልን!

**አቤል ገ/ኪዳን**

ክስተቶች የበዙበት ሳምንትን ነው ያሳለፍነው። ከጎንደሩ ክስተት ጀምሮ ወራቤ ላይ የተፈጸመውን አስከትሎ አዲስ አበባ የደረሰው ሁኔታ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነበር። እንዲሁም ልብ የሚያደሙ እና አንገትን የሚያስደፉ ነገሮች ለበዙባት አገር የሰሞኑ ክስተት ደግሞ አዲስ ሀዘን ነበር። ብዙሃን ሞተዋል፤ የተቀደሱ የአምልኮ ስፍራዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ብዙ ንብረትም ወድሟል። የሚመለከታቸው አካላት በዚህ ዙሪያ የተጣራ ማብራሪያ እስኪያቀርቡ ድረስ ጉዳዩ ይቆየንና በሰሞኑ ክስተት መሀል ያየናቸውን ብርሃናዊ ነገሮች አጉልተን እናውራ፡፡

በኢድ እለት የቀይ ሽብር ሰማዕታት ሐውልት አካባቢ ትርምስ ተፈጥሮ ነበር። በዚህ ወቅትም ጥቂት ግለሰቦች ስሜታዊ ሆነው አንዳንድ ያልተገቡ ተግባራትን ሲከውኑ አይተናል። በዚህ ትርምስ መሀል ግን አንድ ወንድም ህዝብን ሲያረጋጋ እና ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑ ለማድረግ ሲጥር ታይቷል። በመሰረቱ ልናውቀው የሚገባ አንድ ነገር አለ። ግለሰቡ ያደረገው ነገር አዲስ አይደለም። ተአምርም አይደለም። እንደ አንድ ጥሩ አማኝ እና እንደ አንድ ሰላም ወዳድ ዜጋ ሊያደርግ የሚጠበቅበትን ነገር ነው ያደረገው። ለአንድ ሙስሊም ይህን ማድረግ የዘወትር ተግባሩ ነው ተብሎም ይታመናል። አስተምህሮውም እንደዚያ ነው። ስለዚህ ያደረገው በተለየ ሁኔታ ሊደነቅ የሚገባው አልነበረም፡፡

ይህን ሰው የምናደንቀው ግን ከምንኖርበት ዘመን አንጻር ነው። ያለፉት ጥቂት አመታት አገራችን መካሪ ሽማግሌዎቿ ያለቁባት እስኪመስል ድረስ በየቦታው ሁከት የሚፈጠርባት አገር ሆና ከርማለች። የዚህ መንስኤው ሁላችንም ከደረጃ በመውረዳችን ነው። የሰላም ሀይል የሚባል ተመናምኖ ሁሉም ወገን ወገኑን መርጦ ይዞ የሚፋጅባት አገር የሆነችው እንደዚህ ወንድም አይነት ተረጋጉ የሚል ሰው በመጥፋቱ ነው። ያሉን የሃይማኖት አባቶች በአደባባይ በቃል ከመገዘት እና ከማሳሰብ በላይ በቦታው ተገኝተው እንደዚህ እንደ ወንድማችን ወዲህ ወዲያ ተሯሩጠው እና ተናንቀው ሰላምን ማውረድ የሚችሉበት አቅም የላቸውም። አቅም ያለው በበኩሉ አንቂ እና አደራጅ ሆኖ ለሁለት እና ለብጥብጥ ሲያሰማራ ነው የሚውለው። ታዲያ በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ በቦታው ላይ ተገኝቶ፤ ወዲህ ወዲያ ተሯሩጦ አደብ ግዙ ያለን ሰው ማመስገናችን በእጅጉ ተገቢ ነው፡፡

ልብ እርጉ፤ ግለሰቡ ያደረገው የሚጠበቅበትን ነገር ነው። ነገር ግን በየቦታው ሁከት የበዛው ልክ እንደሱ የሚጠበቅባቸውን ነገር የሚያደርጉ ሰዎች ባለመኖራቸው ነው። እንዲያውም ለዚህ የሚስማማ አባባል አለ። ተናጋሪው ታላቁ ማርቲን ሉተር ኪንግ ነው ይባላል። “The world suffers a lot. Not because of the violence of bad people but because of the silence of good people.” ይላል አባባሉ። ትርጓሜውም “ዓለም እየተሰቃች ያለችው በክፉዎች አመጽ ሳይሆን በመልካም ሰዎች ዝምታ ነው” እንደማለት ነው። እውነት ነው። በመልካሞች ዝምታ የተነሳ አመጸኞች ጉልበተኛ ሆነዋል። ይህ ወንድማችን ከመልካም ሰዎች አንዱ ነው። እሱ ዝም ቢል ኖሮ ሁከት እየፈጠሩ ለነበሩ ምንኛ ጉልበት በሆናቸው ነበር:: ነገር ግን ዝም አላለም። የአቅሙን አደረገ። ሁከቱ እንዳይስፋፋ የድርሻውን ተወጣ። ለዚህ ተግባሩ ደግሞ አክብሮት ይገባዋል። ለከርሞው ሰላሟ እንዲሰፍን ከፈለግን በየቦታው እንደሱ ያሉ መልካም ሰዎች ዝምታቸውን እንዲሰብሩ እና ከታዛቢነት እንዲወጡ ማድረግ አለብን። ያኔ ነው አገር ሰላም የምትሆነው፡፡

ሌላኛዋ መልካም እህት ደግሞ በወቅቱ ተቃውሞ እያሰሙ የነበሩ ወጣቶች ሁከትን ሳይቀላቅሉ ተቃውሞአቸውን እንዲያሰሙ ስትወተውት የነበረች ናት። ይህ ደግሞ ስልጣኔ ነው። መቃወም መብት ነው። ሁከት መፍጠር ግን መብት አይደለም። እኛ ጋር ብዙውን ጊዜ ሁለቱ ይደባለቃሉ። ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ ወደ አመጽ ለመሻገር ብዙ አይፈጅበትም። ለብጥብጥ ቅርብ የሆንን ሰዎች ብዙ ነን። እርግጥ ይህ የሚሆነውና ብዙው ሰው ወደ ሁከት የሚቻኮለው ለሰልፍ የወጣበትን ጉዳይ ምንነት እና አላማ በቅጡ ስለማያውቀው ነው። ሁሉም የየራሱ ብሶት ይዞ ይወጣል። ብሶቱ የጸናበት ሰልፉን ወደ ሁከት ይለውጠዋል። ሁከት ደግሞ እንደ ሰደድ እሳት ነው። ቶሎ ይስፋፋል። በተለይም እኩይ አላማ ይዞ የሚሰራበት ሰው ሲገኝ በቶሎ ይቀጣጠላል። ያቺ እህት ይህን የተረዳች ነች። ከቤቷ የወጣችበትን አላማ ታውቀዋለች። የምትቃወመውን የምትቃወምበትን ምክንያት እና የምትቃወምበትን መንገድ አልረሳችም። ስለዚህም “የሰው ንብረት አትንኩ የፈጣሪን ስም ብቻ ጥሩ” እያለች አብረዋት ያሉት ሰዎች ያለ ምንም ትርምስ ተቃውሞአቸውን እንዲያሰሙ ለማድረግ የአቅሟን ስትጥር ነበር። እንዲህ ያሉ የሰላማዊ ትግል የገባቸው ሰዎች በአገሪቱ መበርከት አለባቸው። እንዲህ ያሉት ሲበዙ ነው ዛሬ በየስርቻው ተወሽቀው የወንበዴ ስራ እየሰሩ ነጻ አውጪ ነን የሚሉ ወሮበሎች ሊጠፉ የሚችሉት፡፡

ሶስተኛዋ ደግሞ ህግ አስከባሪ ናት። በእለቱ ለመደበኛ ተልእኮ የተሰማራች ነበረች። ከተፈጠረው ትርምስ በኋላ ብዙ ህጻናት ከወላጆቻቸው ተጠፋፍተው ብዙ ጭንቀት ተከስቶ ነበር። በዚያ ሰዓት ግን እሷ አንዲትን ህጻን አቅፋ እያረጋጋች፤ ስራዋንም እየሰራች ነበር። የሷ ስራ ህግን ማስከበር እና በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ማድረግ ነበር። ነገር ግን ሰብዓዊነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ሲገጥማት ከስራዋ ሳትዘናጋ የሰውነት ልኳን አሳየች። ለሷ ከፖሊስነቷ በላይ እናትነቷ ፤ እህትነቷ ፤ ሴትነቷ ብሎም ሰውነቷ ቀድሟልና ሰብዓዊነትን ስራዋ አደረገች። አሁን ችግር የሆነብን ከሰው ይልቅ ብሔራቸውን፤ ሃይማኖታቸውን፤ ቋንቋቸውን፤ ብሔራቸውን፤ መሬታቸውን፤ ስልጣናቸውን የሚያስቀድሙ ሰዎች በዝተው ነው። ኢትዮጵያውያን ለሰው ቅድሚያ መስጠት ካልጀመርን ለውጥን ማምጣት እንደማንችል ማወቅ አለብን። ስለ አንዲት ነፍስ የማይጨነቅ ሰው ስለሺዎቹ ሊጨነቅ አይችልም፡፡

ስናጠቃልለው፤ ያለንበት ጊዜ አስቸጋሪ ነው። ወዲያም ወዲህም ብንዞር የሚታየው እና የሚሰማው ነገር የሚያበረታ አይደለም። የሚታይ የሚሰማ በጎ ነገር ጠፍቶ አይደለም። በጎ የሚደርግም ሰው ጠፍቶ አይደለም። ይልቁንም በጎዎቹ ዝምታ ስለመረጡ ነው። ስለዚህ እንዲህ እንደጠቀስናቸው ሰዎች ያሉ በጎ የሚያስቡ እና ዝምታን ሳይመርጡ ያሰቡትን በጎነት በተግባር የሚያደርጉ ሰዎች ጥቂትም ቢሆኑ እነሱን ማመስገን አለብን። የበጎነት ትንሽ የለውም። የፈጸሙት ተግባር የተለመደ እና ምንም ሰው ሊያደርገው የሚገባ ነገር ቢሆንም ዛሬ ዛሬ የተለመደ እና ማንም ጤነኛ ሰው ያደርገዋል የምንለው ነገር ሁሉ ነውና እየጠፋ ያለው እንዲህ አይነቱን ነገር ሲደረግ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በቀጣይ እንዲህ አይነቱ ሰው እና እንዲህ አይነቱ ተግባር ተበራክቶ አስደናቂ መሆኑ እስኪቀር ድረስ ግን እንዲህ ያሉትን በጎዎች ያብዛልን ብለን ጽሑፋችንን ቋጨን፡፡

## ነፃ ሃሳብ

# እንደ አባቶቻችን አገርም፣ ታሪክም፣ ኢትዮጵያዊም እንሁን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ለዘመናት አገርን በእናትነት ወክለን ስንዘፍንና ስንቀኝ ኖረናል። አዎ አገር እናት ናት። እናት ልጆቿን አምጣ እንደምትወልድና፣ በጀርባዋ አዝላ፣ በክንዷ ታቅፋ ቀን እንደምታወጣ ሁሉ፤ አገርም የዜጎቿ መብቀያ አብራክ ናት። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደሆነ ሁሉ አገርም በብሔርና በሃይማኖት፣ በቋንቋና በቀለም የተዋሀዱ ብዙ አይነት ልጆች አሏት። የትኛውም ልጅ በወለደችው በእናቱ ላይ ጨክኖ አያውቅም። ታዲያ የእኛ በአገር ላይ መጨከን ከየት የመጣ ነው? ከሌላት ላይ ሰጥታ ቀን ያወጣችንን አገራችንን ዛሬ ስንፈረጥም ክንዳችንን እሷ ላይ ማሳየታችን ምን የሚሉት ስልጣኔ ነው? ብዙዎች የአገራቸውን ፍቅር መሬቷን በመሳም ይገልጻሉ፣ ብዙዎች የሕዝባቸውን ውለታ በጎ በማድረግ ይመልሳሉ። እኛ አገር ሲሆን ይሄ ሁሉ ሌላ ነው። ተምረን አገራችንን በወጉ አገልግለን አናወቅም። መሰላል ሆኖ ከፍ ያደረገንን ሕዝባችንን በነውረኛ ድርጊት ዝቅ ማድረግ አመላችን ሆኗል። ብዙዎቻችን የእናት ጡት ነካሾች ነን። ለድሀ አገራችን የሚሆን አንዳች ነገር የለንም።

ኢትዮጵያ አገራችን ታሪክ ያላት አገር ናት። አባቶቻችን ዓለምን ምሰሶ ሆነው ያቆሙ ናቸው። የእኛ በነውር መቆም ምን የሚሉት ነው? በእውቀትና በጥበብ፣ በሀይልና በማስተዋል ዓለምን ከኋሉ አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት። የአገራችንን ትላንታዊ መልክ ለማናውቅ ይሄ ቀልድ እንደሚሆን አውቃለሁ። የኢትዮጵያን መነሻ፣ የሕዝቦቿን ድሮአዊ ታሪክ ለማያውቅ ይሄ እንደማይዋጥለት አውቃለሁ። እውነቱ ግን ይሄ ነው። እኛ ታላቅ ምድር ላይ የተፈጠርን ታላቅ ሕዝቦች ነን። እኛ በኩሩና በስልጡን፣ በጀግና ማህጸን እቅፍ ውስጥ የበቀልን የዚህ ዓለም ጌጦች ነን። መልካችንን በገዛ እጃችን አናበላሽ። ትላንት ለዓለም መፈጠር ምክንያት ነበርን፣ ይሄን ዓለም ውብ ያደረገው የእኛ መልክ ነው። ይህ መልክ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት የሚገለጥ መልክ ነበር። ይሄን ዓለም በዚህ ልክ ያቆመው የእኛ መኖር ነበር። የእኛ መኖር ለብዙዎች መኖር ዋስትና ሆኖ ዛሬም ድረስ ይኖራል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ኢትዮያዊነት የኩራት ምንጭ ነው። ከአምና እስከ ዘንድሮ፣ ከዘፍጥረት እስከ አሁን ድረስ ብዙ ቦታ ላይ በማይታመን ትልቅነት ውስጥ ነበርን። ዛሬስ ምን ነካን? በአንድነት መቆም ለምን ተሳነን?

በየትኛውም መመዘኛ ብታዩት የአገራችን የስልጣኔና የእውቀት ምህዳር በድሮነት ውስጥ አለ። አሁን ላይ በብዙ ነገራቸው የዓለምን የስልጣኔና የኢኮኖሚ በትር ይዘው የሀያልነት ማእረግ ያገኙ ሁሉ አንድ ወቅት ላይ ታሪክ ያልነበራቸው ከነጭራሹ አገር ለመባል ያልበቁ ነበሩ። በሌላ ቋንቋ ከእኛ ኋላ የተፈጠሩ፣ ከእኛ ኋላ አገር የሆኑ ናቸው እያልኳችሁ ነው። እኔና እናንተ በጥንት አባቶቻችን አጥንትና ደም ለዚች ዓለም የስልጣኔ ብርሃንን የለኮስን በኩራን ነበርን። የስልጣንና የአለቅነትን ጫንቃ የያዝን የቅድመ ዓለም ፋና ወጊዎች ነበርን። ከዚህ እዛ ድረስ የሚደርስ የስልጣን፣ የሞገስና የተፈሪነት ሀይል ነበርን። በትልቅ ዓለም ላይ ትልቅነትን የከተብን በኩረ ዘፍጥረቶች እንዲህም ነበርን። ዛሬ ግን ያ የአባቶቻችን መንፈስ ርቆን መለያየትን እንደ ትልቅ ስልጣኔ ቆጥረን ለብቻ እየተራመድን ነው። ሰው ለብቻው ሲቆም፣ ሰው ለብቻው ሲራመድ ምንም ነው። የምንበዛው፣ የምንፈራው፣ ሀይል የምናደርገው በአንድነት ስንቆም ነው። አገር የምንፈጥረው፣ ታሪክ የምንሰራው፣ ለትውልድ ቅርስ የምናስቀምጠው መነጋገርና መግባባት ስንችል ነው። የኢትዮጵያን ውለታ የምንከፍለው፣ ድሀ ሕዝባችንን ከድህነት የምናወጣው ተግባብተን መኖር ስንችል ነው።

በምንምነት ውስጥ አክሱምን ሰርተናል። በምንምነት ውስጥ ላሊበላን አንጸናል። በምንምነት ውስጥ ለሰው ልጅ እሳቤ የማይቻሉ ታላላቅ ገድሎችን ለብቻችን ተወጥተናል። ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ትልቅነት አለ? ከዚህ በላይ ምን ፍጹምነት ይገኛል? ዓለም እኮ የኢትዮጵያን ያክል ምንም የላትም። ግን በምንምነት ውስጥ ሁሉም አገራት፣ ሁሉም መንግስታት ቀድመውን ባሪያ አድርገውናል። ይሄ ሁሉ የሆነው ለብቻ በመቆማችንና ስር በሰደደ የብሔር ፖለቲካ በመታመማችን ነው። አባቶቻችን አክሱምን ሲሰሩ፣ ላሊበላን ሲያንጹ ብሔር አልነበራቸውም። አባቶቻችን ጣሊያንን አሸንፈው ዓድዋን ሲፈጥሩ ብሔር አልነበራቸውም። አባቶቻችን በካራማራና በኡጋዴን በሌሎችም ስፍራዎች ድል ሲቀዳጁ ብሔር አልነበራቸውም። የአባቶቻችን ብሔር ኢትዮጵያዊነት ነበር። እኛም ድሮነትን ካልተላበስን፣ እንደ አባቶቻችን በኢትዮጵያ ስም መማል ካልጀመርን እንቅፋቶቻችን ይበረክታሉ እንጂ አይቀንሱም። እንደ አባቶቻችን ኢትዮጵያዊነትን ከፊት አስቀድመን ከኋላ እስካልተከተልን ድረስ ታሪክ መስራት አይቻለንም። እኛ ብሔርና እኔነትን ከፊት አስቀድመን ኢትዮጵያዊነትን ያዘገየን ነን፣ እኛ ዋጋ ካላቸው ባህላዊ እሴቶቻችን ይልቅ በሴራ የተጎነጎነ ፖለቲካዊ አካሄድን የመረጥን ነን። በዚህ ውስጥ ደግሞ ፊተኝነት የለም። በዚህ ውስጥ ደግሞ ማሸነፍ የማይታሰብ ነው።

ትላንት ላይ ሁሉም ቦታ ነበርን። ትላንት ላይ ተዐምር የሰሩ እጆች የእኛ ነበሩ። ትላንት ላይ ከሁሉ የበረቱ ክንዶች የእኛ ነበሩ። በምንምነት ውስጥ ከምድር አልፈን ከህዋ አካላት ላይ ስልጣኔአችንን ያሳረፍን ታላቅ ሕዝቦች ነበርን። ትልቅ ነበርን፤ ብዙዎች ያጨበጨቡልን፣ ብዙዎች እኛን ለመሆን የሚመኙ የዛኛው ትውልድ ምልክቶች ነበርን። አገራችን ኢትዮጵያ ለብዙ አገራት የስልጣኔ ምንጭ ሆና የሰነበተች ቢሆንም ዛሬ ላይ ግን በብዙ ችግሮች ውስጥ የምትገኝ አገር ሆናለች። ከፊትና ከኋላዋ ብዙዎች የተነሱባት ጊዜ ላይ ነን። የጥንቱ የአባቶቻችን አንድነትና ህብረት ግድ የሚልበት ሰዓት ላይ እንገኛለን። በትላንት ውስጥ ያለችውን የአባቶቻችንን ኢትዮጵያ ዳግም ለመፍጠር የአሁኑ ትውልድ ምን እየሰራ እንደሆነ ማጤን ይገባዋል። የትላንትናዋ ኢትዮጵያ ዝም ብላ የተፈጠረች፣ ዝም ብላ ስልጣኔን ያገኘች ሳይሆን በአባቶቻችን የአንድነት ክንድ፣ የህብረት እሳቤ የተፈጠረች ናት። ዛሬ ላይ ትልቅ ነበርን ብለን አፋችንን ሞልተን በኩራት የምንናገረው ትልቅ አገር ባስረከቡን አባቶቻችን ብርታት ነው። ብኩርናችንን ይዘን እንቆይ ዘንድ እኛ የዛሬው ትውልድ የአባቶቻችንን እውነት መከተል ይኖርብናል።



የአባቶቻችን እውነት ምን ነበር? የአባቶቹ እውነት የገባው ወጣት ዛሬ ላይ ታሪክ ከማውራት ወጥቶ ታሪክ እንደሚሰራ አልጠራጠርም። የአባቶቹን እውነት የተረዳ ትውልድ ዛሬ ላይ ለልጆቹ የምትሆንን ሰላማዊ ሀገር ለመፍጠር አቅም ያንሰዋል ብዬ አላስብም። የአባቶቻችን እውነት አንድነት ነበር። የአባቶቻን እውነት ፍቅር ሰላም ነበር። የአባቶቻችን እውነት መተሳሰብ ነበር። የአባቶቻችን እውነት ፈርሀ እግዚአብሔር ነበር። የአባቶቻችን እውነት ኢትዮጵያዊነት ነበር። የእኛስ እውነት ምንድነው? ዛሬ ላይ እንደ ሕይወት መርህ የምንከተለው እውነታችን ምን ይሆን? የምንማረው፣ የምንሰራው፣ አግብተን የምንወልደው ለምንድነው? ወጣት የሆንነው፣ እንደ ዜጋ የምንጠራው ለምንድነው? የተፈጠርነው፣ ሰው የሆንነው ለምንድነው? ይሄን ጥያቄ እንመልስ። የትውልዱ ምርጥ ጥያቄ ይሄ ነው። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ራሳችንንም አገራችንንም እንፈልግ። የምንፈልጋት ኢትዮጵያ በዚህ እውነታችን ውስጥ ናት።

በሀሳብ ዘምና፣ በስልጣኔ ቀድማ ለዓለም ብኩርናን ያስተማረች፣ የብርሃን ችቦ ሆና ለሰው ዘር ሁሉ የበራች አገር ዛሬ በሕዝቦቿ አንድነት ማጣት ልዕልናዋን ስትነጠቅ ማየት ያማል። የትላንት አባቶቻችን ባልሰለጠነ ዓለም በባዶ እግራቸው እየሄዱ ነው ታላቅነትን የሰጡን። ይሄን ሲያደርጉ ግን ፍቅርን ያውቁ ነበር፤ ከሁሉም ትልቁን እግዚአብሔርን ይፈሩ ነበር። በራሳቸው መንገድ በራሳቸው እውነት ተጉዘው ነበር ዛሬን የፈጠሩልን። እኛ የዛሬዎቹ የአባቶቻችን የቀና መንገድ እያለ ክፉት በዋጀው በሌሎች መንገድ የምንሄድ ነን። ልባችንን ከፍቅር፣ እጃችንን ከስራ አቀያይመን በትችትና በወቀሳ የቆምን እንዲህም ነን። እውነት ነው ትልቅ ነበርን ትልቅ የሆነው ግን ተለያይተን ስለቆምን በዘርና በብሔር ስለተከፋፈልን አይደለም። የትልቅነታችን ምንጭ አንድነታችን ነበር። የትልቅነታችን መሰረት ሕዝባዊነት ነበር። የአባቶቻችንን ሀቅ እንውረስ ስል እማጸናችኋለሁ። አሁን ካለንበት ክፉ አገራዊ መልክ እንወጣ ዘንድ፣ አሁን ካለንበት ድህነትና ኋላ ቀርነት እንወጣ ዘንድ በጽድቅና የሚኖሩትን የአባቶቻችንን ነፍስ መጋራት ይኖርብናል። የአባቶቻችን የትላንት መልክ በእኛ በልጆቻቸው ላይ መመለስ አለበት። ጣሊያንን ያንበረከኩ የትላንት ጥምር እጆች ዛሬም ያስፈልጉናል። ግብፅና እንግሊዝን ያንበረከኩ የህብረት ክንዶች ያስፈልጉና። ድልን የሚጽፉ፣ ብስራት የሚናገሩ አንደበቶች እንሻለን።

በዓለም አደባባይ ያጀገኑን፣ ስማችንን በወርቅ ቀለም ያጻፉ ትላትናዊ ብዙ መልኮች አሉን። እኚህ ሀበሻዊ መልኮች ዛሬም ያስፈልጉናል። ሊወሩን ባኮበኮቡ፣ አንድነታችንን ጠልተው ጥርሳቸውን በነከሱብን ጠላቶቻችን ላይ መደገም አለበት እላለሁ። የነገ ትልቅነታችን ያለው በዛሬያችን ውስጥ ነው። ዛሬ ላይ ለነገ ስንቅ የሚሆኑ መልካም ተግባራትን በመከወን ራሳችንን ለትልቅነት ማዘጋጀት ይኖርብናል። ነገ ለምንናፍቀው አገራዊ ልዕልና ስንል ዛሬን በዋጋ መኖር ግድ ይለናል። ትልቅ ነበርን እያልን ታሪክ ከማውራት ወጥተን ታሪክ ወደ መስራት መሸጋገር የዛሬው ትውልድ የቤት ስራ መሆን አለበት። ከትላንት እስከ ዛሬ ታሪክ ስናወራ ገድል ስንዘክር ኖረናል አሁን ግን ታሪክ ወደ መስራት የምንሸጋገርበት የድርሻችንን የምንወጣበት ምቹ ጊዜ ላይ ነን። ልጆቻችን የአያቶቻቸውን ሳይሆን የእኛን የአባቶቻቸውን ታሪክ መስማት ይፈልጋሉ። እኛ በአባቶቻችን እንደኮራን ሁሉ ልጆቻችንም በእኛ የሚኩሩበትን ታላቅ እና ደማቅ ሕዝባዊ ታሪክ መጻፍ አለብን። ታሪካችን ደግሞ ከአሁን የሚጀምር ነው። ታሪካችን ደግሞ በስራ፣ በተግባር የሚገለጽ ነው።

ታሪክ ለመጻፍ ጦርና መሳሪያ መታጠቅ አይጠበቅብንም። ታሪክ ለመስራት ስልጣንና አለቅነት ግድ አይለንም። ታሪክ ለመጻፍ ጦር ሜዳ ዘምተን ከጠላት ጋር ተዋግተን መሞትና መግደል አይኖርብንም። ታሪክ በብዙ መንገድ ይሰራል። ተማሪ የሆነ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት በማምጣት አገርና ሕዝቡን በታማኝነት በማገልገል ታሪክ መስራት ይችላል። መምህሩ አገር ተረካቢ የሆኑ ታማኝና አስፈላጊ ተማሪዎችን በማውጣት የድርሻውን መወጣት ይችላል። የፖለቲካ ሀይሎች ተነጋግሮ በመግባባት ታሪክ መስራት ይቻላቸዋል። እንደ ዜጋ ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን ታሪክ ለመስራት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን። መልካም በማድረግ፣ መልካም በማሰብ፣ የዜግነት ግዴታችንን በመወጣት ታሪክ መጻፍ ይቻለናል። ከፊታችን ብርሃንና ጨለማ የቀላቀለ ድንግዝግዝ መልክ አለ። ከፊታችን እየበራ የሚከስም፣ እየከሰመ የሚበራ ቅይጥ ብርሃን አለ። በእኔና በእናንተ የተሳለ ጉራማይሌ መልክም ከፊታችን አለ። ሁሉም የሚጠራው ሁሉም የሚስተካከለው በእኛ ነው።

ምርጧ ኢትዮጵያ በምርጥ ሀሳባችሁ ውስጥ ናት። ምርጧን ኢትዮጵያ በምርጥ ሀሳባችሁ ፍጠሯት። ብዙዎቻችን ጥሩ ነገርን ከሌላ የምንጠብቅ ነን። ጥሩ አገር ስልጡን ማህበረሰብ እንዲኖረን እንሻለን። ሰላሟ የበዛ በሁሉ ነገሯ የተረጋጋች አገር እንድትኖረን እንፈልጋለን። ከድህነት የወጣ በቀን ሶስቴ የሚበላ ሕዝብ እንዲኖረን ምኞታችን ነው። ግን አንሰራም ግን ለምንፈልገው ነገር ስንለፋ አንታይም። የምንፈልገውን ጥሩ ነገር ሁሉ ከሌሎች የምንጠብቅ ነን። ባጠቃላይ ሳንሰራ ለውጥ የምንፈልግ። ሳንደክም ሳንለፋ ህልማችንን የምንጠብቅ ነን። ይሄ ሞኝነት ነው። ለዛሬ መጠሪያ የሆነችው የአባቶቻችን ኢትዮጵያ በድካማቸው እንደተፈጠረች ሁሉ የእኛም ኢትዮጵያ በእኛ ድካም የምትፈጠር ናት። ጥሩ ነገራችሁን ድካማችሁ ውስጥ ፈልጉት። ለምንም ነገር አቅም ያለን ሕዝቦች ነን። ድህነት ኋላ ቀርነት ምን ማለት እንደሆነ በደንብ እናውቃለን። ችግርና ማጣትን እናውቀዋለን ከዚህ በኋላ ግን በዚህ ክብረ ነክ ውስጥ መኖር አይኖርብንም። የተሻለ ሕይወትን ፍለጋ መስራትና ተነጋግሮ መግባባት ይኖርብናል። በአባቶቻችን እውነት ላይ መራመድ ግድ ይለናል። ሁላችሁም የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመሳል ብዕራችሁን አንሱ። ለሁላችንም የምትበቃ ኢትዮጵያን ለመገንባት ተነጋግረን እንግባባ። ስሜታችንን ሳይሆን እውቀታችንን እናስቀድም። በሀሳብ ማሸነፍን ባህል እናድርግ። ይሄን ካደረግን ታላቋን ኢትዮጵያ መፍጠር ይቻለናል።

# የሃይማት አባቶች ለምዕመናን

ኢያሱ መሰለ

ቤተ-እምነቶች ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር በጸሎት የሚገናኙባቸው፣ ምህረትና ይቅርታ የሚጠየቅባቸው፣ ፍቅርና ሰላም የሚሰበክባቸው፣ ቅዱስ ሥፍራዎች ስለሆኑ በምእመናን ዘንድ ልዩ ክብርና ሞገስ አላቸው። ምእመናን ወደ ቤተ እምነት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲገቡ ጸሎታቸው ወደ ፈጣሪያቸው እንዲያደርሱ ልባቸውን ከሀጽያት ከበደልና ከክፋት አንጽተው ነው። አንዳንዶችም የእግራቸውን ጫማ ሳይቀር አውልቀው፤ እንደየ ሃይማኖታቸው አስተምህሮ ለብሰው ለጸሎት ይሰየሙባቸዋል። በየትኛውም ሃይማኖት ስር ያሉ ምእመናን ግባቸው ጽድቅን ማግኘት ስለሆነ ፈጣሪ የሚወደውን መልካም ሥራ ይሠራሉ።

በአገራችን ብሂል ‹‹ሳል ይዞ ስርቆት፤ ቂም ይዞ ጸሎት›› ይባላልና ሰዎች ወደ ቤተ-አምልኮ ሲሄዱ ተጣልተው ከሆነ ይታረቃሉ፣ በድለው ከሆነ ሀጥያታቸውን ተናዘው ንስሃ በመግባት ልባቸውን አንጽተው “አዲስ” ሰው ይሆናሉ።

ቤተ-እምነቶች መለኮታዊ ሀሳብ ብቻ የሚከናወንባቸው ቦታዎች በመሆናቸው ጸብና ግርግር፤ ዋዛና ፈዛዛ አይስተናጋድባቸውም። በጸሎት ሰዓት አማኞች ለፈጣሪያቸው ምስጋናና ክብር ያቀርቡባቸዋል፤ በመከራ ጊዜ ይሸሸጉባቸዋል። በርካታ ሰዎች በመስጊዶችና በቤተክርስቲያን ሥር እየተጠለሉ የገጠሟቸውን ክፉ ጊዜዎች አሳልፈዋል።

ቤተ-እምነቶች የምህረትና ይቅርታ የሚጠየቅባቸው ቦታዎች እንደመሆናቸው ሰዎች በደል ፈጽመው እንኳ ቢሆን ሸሽተው ወደ ቅጥር ገቢው ውስጥ ከገቡ በፈጣሪ እቅፍ ውስጥ እንዳሉ ስለሚቆጠር ደፍሮ ጥቃት የሚሰነዝርባቸው አካል አይኖርም። ይህ ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዛሬም ያለ ሃይማኖታዊ እሴት ነው።

ከሰሞኑ ታዲያ ከሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችን ያፈነገጡ ጸያፍ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ተመልክተናል። መስኪዶችና ቤተክርስቲያኖች ብዙዎችን በጉያቸው ይዘው እንዳልታደጉ ዛሬ እንደቀላል ነገር ድፍረት በተሞላበት መንገድ ሲቃጠሉ እያየን ነው። ያም ብቻ አይደለም፣ አትግደል የሚለውን የፈጣሪ ቃል ሲማር የኖረ ሃይማኖተኛ በውይይት መፈታት የሚችለውን እዚህ ግባ የማይባል ጉዳይ እያራገበ የገዛ ወንድሙን ሲገድል እየተመለከትን ነው።


ለመሆኑ ሃይማኖተኛ ሆኖ በሌላ ሃይማኖት ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን መፈጸም ምን ያህል ከሃይማኖቶች አስተምህሮ ጋር አብሮ ይሄዳል? እንዲህ አይነቱ አድራጎት በአገር ሰላምና አንድነት ላይ ምን ተጽዕኖ ይፈጥራል? አገርን ለማፍረስ የተዶለተውን ሴራ ለማክሸፍ ከሃይማኖት አባቶችና ከምእመናን ምን ይጠበቃል? የሚሉትንና ሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ ከኦርቶዶክስ ክርስትና እና ከእስልምና አባቶች ጋር ያደረግነውን ቆይታ በዛሬው የ‹‹አገርኛ›› አምድ ዝግጅታችን ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

መጋቤ ካህናት አባ ሃብተጊዮርጊስ አሥራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የገዳማት መምሪያ ዋና ሃላፊ ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት ቤተክርስቲያንና መስኪድ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር አንድ ናቸው። ሁለቱም እንደየ ሃይማኖታቸው አስተምህሮ ተከታዮቻቸው ሰማያዊውን ጸጋ ለማግኘት ቃልን የሚሰሙባቸው፣ የሚጸልዩባቸው፣ የሚሰግዱባቸው ሥፍራዎች ናቸው። ሁለቱም ሃይማኖቶች “ወንድም ወንድሙን አይበድል” ብለው ያስተምራሉ ይላሉ። መዋደድ፣ መተዛዘን፣ መደጋገፍ ሁለቱም ሃይማናቶች ከሚጋሯቸው እሴቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ሰሞኑን በጎንደርና በወራቤ አካባቢ ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ግጭት መፈጠሩ የሚያሳዝን ነው፤ በሰው ህይወትና በሃይማኖት ተቋማት ላይ ጉዳት አስከትሏል። እንደርሳቸው አባባል የሃይማኖት ሰዎች በዚህ ልክ ግጭት ይፈጥራሉ የሚል እምነት የላቸውም። ከግጭቱ ጀርባ የፖለቲከኞች እጅ አለበት ባይ ናቸው።

የሃይማኖት ተቋማትና ምእመናንን ኢላማ ያደረጉ የፖለቲካ ነጋዴዎች በሚፈጥሩት ሴራ፤ አንዳንዶቹ ተልእኮ ይዘው ሌሎችም ሁኔታው ሳይገባቸው ግጭት እየፈጠሩ ለዘመናት ተከባብሮ የኖረው ምእመን እንዳይተማመን የማድረግ ሥራ እየሠሩ ናቸው።

የፖለቲካው ጉዳይ የሚቀጣጠለው የሃይማኖት ጦርነት ስናስነሳ ነው በሚል አስልተው፣ አቅደውና



መጋቤ ካህናት አባ ሃብተጊዮርጊስ አሥራት


ጎንደር የተፈጸመው ድርጊት እንደ ሰብዓዊ ፍጥረትም እንደ ባለሃይማኖትም ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም። ችግሩን እዚያው መፍታት ሲቻል ሌላ ቦታ ሄዶ አጸፋ መስጠት ግን ጉዳዩን ለማባባስ እና ለማስፋፋት ካልሆነ በስተቀር መፍትሄ አይሆንም

ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ስላሉ ነው። እነዚህ ጥቂት ሰዎች የብዙኋኑን የልብ ትርታ እያዳመጡ ለስሜቱ ስስ የሆኑ ጉዳዮችን በመነካካት ትርምስ እንዲፈጠር እየጣሩ ናቸው። ያ ባይሆን ኖሮ ጎንደር ላይ የተቀሰቀሰው ግጭት በቀላሉ በተፈታ ነበር፡፡

ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጉዳይ የጎላ ልዩነት አይፈጥርብንም፤ ሙስሊምና ክርስቲያን በማህበራዊ ህይወታችን ተለያይተን አናውቅም። ሀዘንና ደስታን እየተጋራን ብዙ ዓመታትን አብረን ኖረናል፤ ይህ ወደ ፊትም የሚቀጥል ነው።

ቤተክርስቲያኖች ሲሰሩ ሙስሊሙ በገንዘብም በጉልበትም ይረዳል፤ መስኪዶችም ሲሰሩ ክርስቲያኑ እንደዚያው ይረዳል፤ ዛሬ እሚቃጠሉ ቤተ-እምነቶች የአንድ እምነት ተከታዮች ብቻ የሠሯቸው አይደሉም፤ ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያኖች በመስጊዶች መቃጠል ይቆጫሉ እንጂ አይደሰቱም፤ እውነተኛ ሙስሊሞችም በቤተክርስቲያኖች መቃጠል ያዝናሉ እንጂ አይደሰቱም።

ተቃቅፎና ተደጋግፎ እዚህ የደረሰ ማህበረሰብ ዛሬ የፖለቲካ ሴረኞች በሰሩት ደባ ሊለያይ አይችልም። ምእመኑ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያን የማፈራረስ ሴራ አንግበው የሁለቱን ታላላቅ ሃይማኖት ተከታዮች ለማባላት ተግተው እየሠሩ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል።



ሼህ ሙሃመድ አሊ ሙሳ

አለመግባባትና ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ሃይማኖታዊ መልክ እያስያዙ ቤተክርስቲያንና መስጊድን መቃጠል ኢትዮጵያን ወደ ከፋ ትርምስ ለማስገባት የታሰበ የፖለቲከኞች አሻጥር መሆኑን ምእመኑ በሚገባ መረዳት ይኖርበታል።

ጎንደር የተፈጸመው ድርጊት እንደ ሰብዓዊ ፍጥረትም እንደ ባለሃይማኖትም ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም። ችግሩን እዚያው መፍታት ሲቻል ሌላ ቦታ ሄዶ አጸፋ መስጠት ግን ጉዳዩን ለማባባስ እና ለማስፋፋት ካልሆነ በስተቀር መፍትሄ አይሆንም።

ስህተቱን ማረም እንጂ ስህተቱን በስህተት መድገም ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ አይደለም። ፈጣሪ የሚወደው ቂምና በቀልን ሳይሆን ሰላምና ፍቅርን ነው። ሁላችንም የአዳምና የሄዋን ልጆች ነን። እርስ በእርሳችን የምንጋጭ ይመስለናል እንጂ ግብ ግብ የያዝነው ከፈጣሪችን ጋር ነው። ምክንያቱም የሚቃጠሉት ቤተ-እምነቶች ፈጣሪ የሚመሰገንባቸው ናቸው። ሰው ፈጣሪውን የሚያመሰግን እንጂ የሚያሳድድ መሆን የለበትም።

የሚቃጠሉትን ቤተ-እምነቶች ነገ የሁለቱም እምነት ተከታዮች ተባብረው ይሠሯቸዋል እንጂ መስኪድ በተቃጠለበት ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን አይሠራበትም፤ ቤተክርስቲያን በተቃጠለበት ቦታ ላይም መስጊድ አይሠራበትም።

መተኪያ የማይገኝለት ክቡር የሆነው የሰውልጅ ነፍስን ግን መመለስ አይቻልም። “አትግደል” የሚል ሃይማኖት እየተከተሉ ነፍስ ማጥፋት ፍጹም ሀጥያት ነው። እውነተኛ የሀይማኖት ሰው ወንድሙን አይጠላም፤ አይገድልም፤ ቤተ እምነትን አያቃጥልም፡፡

ቤተክርስቲያንና መስጊድ የጸሎት ቦታ ብቻ ሳይሆኑ ችግረኞች የሚረዱባቸውና የሚሸሸጉባቸውም ጭምር ናቸው። መጋቤ ካህናት አባ ሃብተጊዮርጊስ ቀደም ሲል ስለተከሰተ አንድ ጉዳይ የሰሙትን እንዲህ ይናገራሉ

‹‹መርካቶ የሚገኘው ራጉኤል ቤተክርስቲያን መጀመሪያ የነበረው እንጦጦ አካባቢ ነበር፤ ታቦቱ ከእንጦጦ ተነስቶ መርካቶ ሲገባ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ አለመግባባት ይፈጠራል። ጉዳዩ አንድ፣ ሁለት እያለ ወደ ጸብ ያድግና እዚያው መርካቶ በርካታ ሰዎች ሆነው የተወሰኑ ሰዎችን ማጥቃት ይጀምራሉ። በዚህን ጊዜ ጥቃቱ የበረታባቸው ሰዎች ወደ አንዋር መስጊድ ዘለው ይገባሉ። በወቅቱ መስጊዱ ውስጥ የነበሩ ኢማሞች ሸሽቶ መስጊድ የገባ ሰው አይነካም›› ብለው እንደታደጓቸው መስማታቸውን ነግረውናል። ቤተክርስቲያንም ይሁን መስጊድ ሰዎች ከሚያሳድዷቸው ጠላቶቻቸው ሸሽተው የሚሸሸጉባቸው ናቸው። ለሰዎች ጥላ ከለላ ናቸው። እንደ ሃይማኖታዊ እሴታችን ሸሽቶ በሃይማኖት ተቋማት ቅጥር ግቢ የገባ ሰው ማንም አንቆ አያወጣውም። ዛሬ ቤተ-እምነቶች ለሌሎች ጠባቂ መሆናቸው ተረስቶ ሲቃጠሉ መመልከት ያሳፍራል። አባቶቻችንን ያቆዩልንን እሴቶች ብናከብር አለመግባባትና ግጭቶችን መቆጣጠር እንችላለን።

ወጣቶች ሌላ ሀገር የላችሁምና ለአባቶቻችን እሴቶች ዋጋ ስጡ፤ በስሜት ተነሳስታችሁ ነገ የሚጸጽታችሁን መጥፎ ሥራ አትስሩ፤ በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚሰራጩ ግጭት አባባሽ ምስሎችና መልእክቶችን እያያችሁ አገርን ለማፈራረስ ቀን ከሌት ለሚተጉ አካላት መሳሪያ አትሁኑ። እኛ ኢትዮጵያውያን ተዋልደን፣ ተዛምደን፣ ተጋምደን ያለን ህዝቦች ነን፤ ንቁ፤ ብልህ ሁኑ፤ በጥበብ ተጓዙ›› ብለዋል መጋቤ ካህናት አባ ሃብተጊዮርጊስ፡፡

ሌላው የግል አስተየታቸውን የሰጡን ሼህ ሙሃመድ አሊ ሙሳ ናቸው። ነዋሪነታቸው አዲስ አበባ፣ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ሁለት ነው። እንደ እርሳቸው አባባል ሁሉም ሰው መነሻው አደምና ሃዋን ናቸው። ሰው በጊዜ ሂደት በገባውና በተረዳው መንገድ እንደየራሱ ሃይማኖት ፈጣሪውን ያመልካል። ሙስሊምም ክርስቲያንም በሃይማኖት ይለያዩ እንጂ የሚገዙት ለአንድ ፈጣሪ ነው። ሁሉም ጀነት ለመግባት ፈጣሪ የሚወደውን በጎ ሥራ ይሠራል። ፈጣሪ ክፋትን አይወድም፤ ክፋትን እየሠሩ ሃይማኖተኛ መሆን አይቻልም። ፈጣሪ የሚወደው መረዳዳትን፣ መተጋጋዝን፣ መዋደድን ነው፡፡

አባቶቻችን የሃይማኖት ልዩነታቸውን ጠብቀው በመከባበር በመተዛዘንና በመደጋገፍ ዘመናትን አሳልፈው አገር አስረክበውናል። ሼህ ሙሃመድ አሊ ሙሳ የጥንቶቹ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ፍቅራቸውን ለመግለጽ አደረጉ ስለተባለው አንድ ጉዳይ የሰሙትን እንዲህ ይናገራሉ።

‹‹ሙስሊምና ክርስቲያን በዋና ሃይማታዊ ጉዳዮቻቸው ቢለያዩም በብዙ ነገሮች ይመሳሰላሉ። ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን የገለጹበት መንገድ እንዲህ ነው። ሁለቱም የየራሳቸውን ከብት ባርከው ካረዱ በኋላ በተለያየ ክር እያሠሩ በአንድ እቃ ይቀቅሉታል። ከዚያም ሲበስል አውጥተው የየራሳቸውን ይመገባሉ። እንግዲህ ስጋው አንድ ላይ ሲቀቀል በመረቁ መነካካቱ አይቀርም፤ በማህበራዊ ህይወታቸው ብዙ የሚጋሯቸው ነገሮች እንዳሉ ጥሩ ማሳያ ነው። ልዩነትንም አንድነትም አክብሮ መኖር እንደሚቻል በምሳሌ ያረጋገጡበት ነው። አሁን የሚመጣው ትውልድ የቀደሙት አባቶቹ እንዴት ተስማምተውና ተከባብረው እንደሚኖሩ መረዳት አለበት።

እኔ የምኖረው አዲስ አበባ ቢሆንም ተወልጄ ያደግሁት በድሮው ወሎ ክፍለ ሀገር ነው። ወሎ ሙስሊምና ክርስቲያን በአንድ ቤት ውስጥ ይኖራሉ። የአንድ ቤተሰብ አባላት ግማሹ ሙስሊም ግማሹ ክርስቲያን የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ ስለ እኔ ልንገርህ፤ የመጀመሪያው ልጄ ክርስቲያን ነው። በሃይማኖት ብንለያይም የእርሱ ልጅነት የእኔ አባትነት የሚካድ አይደለም። ታዲያ ማ ማንን ነው የሚያጠቃው፤ እንዲህ ወደ ኋላ እየሄድን ብንመለከት የዓለም ህዝብ በሙሉ የዘር ግንዱ አንድ ነው። ሰው ከሃይማኖት በፊት የነበረ ታላቅ ፍጥረት ነው፤ ሃይማኖት አንዱ ዓላማው ሰው በሰላምና በፍቅር እንዲኖር መጠበቅ ነው።

የሃይማኖት አባቶች ወጣቱን በመምከርና በመገሰጽ በስሜት እየተገፋፉ የሚፈጽማቸውን ድርጊቶች ማስቆም ይኖርባቸዋል። እንዲህ አይነቱ መጥፎ ድርጊት ለአገር አንድነትም ይሁን ለእድገት ጥሩ ስለማይሆን ወጣቶቻችን አገራቸው እንዳትበታተን አስተውለው መጓዝ ይኖርባቸዋል። ጎንደር የተፈጸመውን ድርጊት ሁላችንም አውግዘናል። ነገር ግን ያንን ምክንያት በማድረግ ወራቤ ላይ ቤተክርስቲያኖችን ማቃጠል ችግሩን ከማባባስ ውጭ መፍትሄ አይሆንም። መፍሄው በፍቅር፣ በመከባበርና በመቻቻል መኖር ብቻ ነው፡፡

የሃይማኖት አባቶች ወጣቶችን እየሰበሰቡ ማስተማርና መምከር እንደ ድሯችን ተከባብረንና ተመካክረን እንድናድር ማድረግ ይኖርባቸዋል። መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላትም ችግር ከመድረሱ በፊት ፈጥኖ በመድረስ አጥፊዎችን እየተከታተሉ ርምጃ መውሰድ (ለህግ ማቅረብ) ይኖርባቸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ወጣት ሆይ፣ መልኩን እየቀያየረ ስለሚመጣው ግጭት፤ ሴራ ንቃ!!!

ኢያሱ መሰለ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ አዲስ የለውጥ ምዕራፍ መጀመሯን ተከትሎ ህልውናዋን የሚፈታተኑ በርካታ ተግባራት ሲፈጸሙ ከርመዋል። ከውስጥ እንደ አሸባሪው ሕወሓትና ሸኔ አይነቶቹ፣ ከውጭ የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ህልማቸው የጨነገፈባቸውና የህዳሴው ግድብ ግንባታ እረፍት የነሳቸው ኃይሎች በሚፈጽሟቸው ሴራዎች ኢትዮጵያ ስትፈተን ቆይታለች።

ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ባለፉት ዓመታት የብሔር ግጭቶችን በመቀስቀስ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው እንዳይተማመኑና አንዱ ሌላውን በጠላትነት እየፈረጀ ጥቃት እንዲያደርስበት ሲሠሩ ከርመዋል። በዚህም በርካቶች ለስደትና ለመከራ ተዳርገዋል። ይሁንና ይህ ሴራቸው የሚፈልጉትን ያህል ውጤት እንዳላስገኘላቸው ሲረዱ ደግሞ የሃይማኖት ግጭቶችን በመፍጠር ኢትዮጵያን ወደለየለት ትርምስ ለማስገባት እየጣሩ ይገኛል።

ከሰሞኑ በጎንደር፣ በወራቤ፣ በአዲስ አበባና በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ያየነው ግጭት የዚህ ማሳያ ነው። ከብሔር ግጭት ወደ ሃይማኖት ግጭት መልኩን የቀየረው ስልትና የተቀነባበረው ሴራ ለአገር ህልውና አደጋ ያለው በመሆኑ ወጣቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጉዳዩን በንቃት ሊመለከተው ይገባል።

የኢትዮጵያ ጠላቶች የሃይማኖት ግጭት እንደሚያዋጣቸው አውቀው ወደ ሥራ የገቡት ሕዝቡ በተለይም ወጣቱ በሃይማኖቱ ከመጡበት ወደኋላ አይልም የሚለውን ስስ ስሜቱን ሊጠቀሙበት አስበው መሆኑ ለማናችንም ግልጽ ነው።

በዛሬው የወጣቶች አምድ ዝግጅታችን ወጣቶች በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ ስለሚገኘውና አሁንም ሃይማኖታዊ መልክ ይዞ ስለመጣው የጠላት ደባ ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው? በዚህ አይነቱ የጠላት ሴራ እንዳይጠለፉ ምን ማድረግ አለባቸው? አንድነታቸውንና አብሮነታቸውን እንዴት ማስቀጠል ይገባቸዋል? በሚሉትና በሌሎችም ጉዳች ዙሪያ ሁለት ወጣቶችን አነጋግረን ተከታዩን ጽሁፍ አቅርበናል።

ወጣት እስሌማን አባይ /የአባይ ልጅ/ አገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮችን በንቃት እየተከታተለ ጠቃሚ ሀሳቦችን በማህበራዊ ሚዲያዎች በማጋራት ይታወቃል። በተለይም በህዳሴው ጉዳይ ዙሪያ የግብጾችን ሴራ እና የምዕራባዊያንን ጫና አስመልክቶ በርካታ ቁም ነገሮችን አስነብቦናል። በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚፈጠረው ትርምስ ጀርባ የውጭ ኃይሎች እንደሚገኙበት እምነቱ ነው። በተለይም ግብፅ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ በየጊዜው በጥናት የተደገፉ ሴራዎችን እየፈበረከች በጥቅም ለገዛቻቸው አካላት ማስታጠቋ የአደባባይ ምስጢር እንደሆነ ይናገራል።

ጋዜጠኛ እስሌማን ሰሞኑን የሃይማኖት መልክ ይዞ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የተቀሰቀሰው ግጭት "ኢምፖርት" የተደረገ ወይም የውጭ ኃይሎች ቀርጸው ወደ አገራችን ያስገቡትና በፋይናንስ የሚደግፉት የታሰበበት አጀንዳ ነው ይላል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በሃይማኖትም ይሁን በብሔር ጉዳይ ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ የሚለው እስሌማን የውጭ ኃይሎች በተለይም ግብፅች በውይይትና በንግግር ይፈታሉ እያልን በይደር ያቆየናቸውን ጉዳዮች ወደ ግጭት እንዲያመሩ በማድረግ የኢትዮጵያን ሰላም ለማወክ እየተጠቀሙበት መሆኑን ይናገራል።

ሕወሓት ከስልጣን መልቀቁን ተከትሎ በመንግሥት እና በቡድኑ መካከል የተፈጠረውን ጦርነት የውጭ ኃይሎች እንደጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ሕወሓትን በፕሮፓጋንዳ፣ በፋይናንስ እርዳታ እና በመሳሰሉት በመደገፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ማሳካት የሚፈልጉትን ጥቅም ለማስከበር ሲጥሩ እንደነበር እስሌማን ያስታውሳል።

በወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ ምዕራባዊያን፣ ግብፅና ሱዳን ሲፈጽሙ የነበረው ሴራ የሚታወስ ነው። ሕወሓት በጦርነት በትረ ስልጣኑን መልሶ እንዲቆጣጠርና ጥቅማቸውን እንዲያስከብርላቸው የነበራቸው ፍላጎት ከፍተኛ ስለነበር በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን የማሳደርና ዓለም አቀፍ ሚዲያዎችን እየተጠቀሙ ሥም የማጠልሸቱን ሥራ ሲሠሩ ነበር። ሕወሓት በጦርነት አሸንፎ ስልጣን እንደማይዝ ሲያረጋግጡ ደግሞ ሌሎች አገር ያፈርሳሉ ብለው ያሙኑባቸውን አጀንዳዎች እየቀረጹ በተላላኪዎቻቸው በኩል ለማስፈጸም እየሞከሩ ናቸው ይላል። ከነዚህም አንዱ ሰሞኑን ያየነው የሃይማኖት ግጭት ነው።



ወጣት እስሌማን አባይ

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘጠና በመቶ በላይ አማኝ እንደሆነ ይነገራል . . . በእነርሱ አስተሳሰብ አማኝ ሕዝብ በሃይማኖቱ ከመጡበት አይደራደርም በሚል ወደ ትርምስ ሲከቱት አስበዋል ሊሆን ይችላል**

ጋዜጠኛ እስሌማን እንደሚናገረው፤ በግብጽ አገር የትኛውም ፕሬዚዳንት መጥቶ ቢሄድ ኢትዮጵያ ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የግብፅ የምንግዜም ተቀናቃኝ ተደርጋ መታየቷ አይቀርም። ማንም ይምጣ ማንም ይሂድ ግብፅ በአባይ ላይ ያላት ጥቅም አይቀየርም። ስለዚህ ጥቅማቸውን ለማስከበር የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።

ፕሬዚዳንት አብዱልፈታ አልሲሲ ከአመት በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ጦርነት ውስጥ ሲገባ ቀጣናው ወደ ትርምስ ይቀየራል እያሉ ሲያስጠነቅቁ እንደነበር የሚታወስ ነው ይላል። የጦርነቱ ሁኔታ ብዙም እንደማያስኬዳቸው ሲረዱ ደግሞ የእርስ በእርስ ግጭት የሚቀሰቀስባቸውን ስስ ብልቶች እያጠኑ ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክራሉ።

Egyptian Center for Strategic Study የሚባል አንድ የግብፅ የጥናት ተቋም ከወር በፊት በኢትዮጵያ ጉዳይ ያወጣውን ጥናት ይፋ ማድረጉን እስሌማን ይናገራል። ተቋሙ በግብፅ መንግሥት ፈንድ የሚደረግ ነው። በዚህ ተቋም የሚደረጉ የጥናት ውጤቶች ለግብፅ የደህንነት መሥሪያ ቤት እንዲሁም ለግብፅ ውጭ ጉዳይ



ወጣት ዮሐንስ አበባው

መስሪያ ቤት ይቀርባሉ። ለሕዝብ መገለጽ ያለባቸውም በተለያየ መንገድ እንዲደርሱ ይደረጋል።

ጥናቱ እንደ ሌሎች ጥናቶች መደርደሪያ ላይ የሚቀመጥ ሳይሆን ወደ ተግባር የሚለወጥ ነው። በዚሁ መሰረት ይህ ተቋም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ የተለያዩ ጥናቶችን አድርጓል። ከነዚህ ውስጥ የሶስቱን ጥናቶች ይዘት እንዲህ ያስረዳል። ለምሳሌ «ኢትዮጵያ ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ የፖለቲካ ውክልና እና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች፣ ለዘመናት ያልተሰማው ጩኸት» በሚል አንድ ጥናት አውጥተዋል፤ ሌላው ጥናታቸው ደግሞ «በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደውን ግጭት ሙስሊሞች እንዴት ይመለከቱታል» የሚል ሲሆን፤ ሶስተኛው «እስልምናንና ክርስትናን በመጠቀም በናይል ዲፕሎማሲ ላይ ጫና ለማሳደር ትልቁ የኃይል አማራጫችን ይሆናል» የሚል ነው።

ለነዚህ ጥናቶች መደረግ መነሻቸው አገር ውስጥ ያሉት መልስ የሚሹ ጥያቄዎች ናቸው። ጥናቶቹ በሰላማዊ መንገድ ሊፈቱ የሚችሉትን የሃይማትና የብሔር ጥያቄዎችን ቤንዚል ጠብ እያደረጉበት የእርስ በእርስ ቀውስ ውስጥ እንድንገባ የሚያደርጉ ናቸው።

"ጥያቄ አለኝ" የሚለው አካል ደግሞ አንዳንዱ በማወቅ፤ አንዳንዱም ባለማወቅ በሰላማዊ ውይይት የሚፈቱ ጉዳዮችን የግጭት መንስኤ እያደረገ አጀንዳቸውን ያስፈጽምላቸዋል።

ግብፅ በአባይ ወንዝ ጉዳይ ከየትኛውም የተፋሰሱ አባል አገራት ግንባር ቀደም ተሰሚነት እንደነበራትና ፈላጭ ቆራጭ እንደነበረች፣ ከደርግ መንግሥት መምጣት በፊት ኢትዮጵያ የግብፅ ተባባሪ እንደነበረች፤ በተለይም በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የራሷን ጳጳስ ከመሾሟ በፊት ጳጳሳት በግብፅ ይሾሙላት እንደነበር በጥናቱ ተጠቅሷል። ያ ዘመን ግብፅን ተጽዕኖ ፈጣሪ እንድትሆን አስችሏታል ይላል። በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥትም ኢትዮጵያና ግብፅ እንደቀድሞው ባይሆንም ሰላማዊ የትብብር መንፈስ እንዳላቸው ይገልጻል። አሁንም ሃይማኖታዊ ቅርርቦችን በማጠናከር ለናይል ድርድር መጠቀም በሚያስችል ወሳኝ ሰዓት ላይ እንዳሉ ጥናቱ ያመላክታል።

እስሌማን እንደሚለው በትግራይና በኢትዮጵያ የተለያዩ ክፍሎች ሁሉ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን እያሠሩ እንደነበር በመጥቀስ አሁንም ይህንኑ አጠናክሮ መቀጠል አንዱ አማራጭ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቅሳል።

ጥናታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ለምሳሌ ኦሮሚያ ክልል ከሰማኒያ በመቶ በላይ ሙስሊም ማህበረሰብ አለ ይላል። ቤኒሻንጉልን፣ አፋርን፣ ሶማሌንም እያነሳ ሙስሊሙ ማህበረሰብ አብላጫ አሃዝ እንዳለው ይጠቅሳል። ያም ሆኖ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ ተሳትፎው አናሳ ነው ይላል።

ጽሑፉ አሁንም እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን የሚያነሱ አካላት መኖራቸውን አትቶ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከለሩ እስላማዊ እስካልሆነ ድረስ የግብፅ ፍላጎት ሊሳካ አይችልም ይላል። የተለያዩ ቅንጥብጣቢዎችን ገጣጥመን ስንመለከት ግብፅ ሃይማኖትን መሰረት አድርጋ ኢትዮጵያን የማተራመስ እቅድ እንዳላት እንረዳለን።

በጣም የተቀናጀና የተናበበ ነገር እንዳለም የሚያሳዩ ነገሮች አሉ።

ሌላው የውጭ ተራድኦ ድርጅቶች ይዘው የሚመጡት ተልዕኮ ነው። ከሌሎች አገራት ተሞክሮ ስናይ በእነዚህ ድርጅቶች የሚደረገው ድጋፍ ሰዎችን በተለይም ወጣቶችን በገንዘብ እያማለሉ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት ሲጠቀሙበት ነው። መንግሥት ይህን የሚገታ የህግ አሠራር ቢኖረው ችግሩን ማቅለል ይቻላል ብሏል።

ጋዜጠኛ እስሌማን ወጣቱ ምንም አይነት ጥያቄ ቢኖርበት መፍታት ያለበት እንደአገራችን ወግና ባህል በምክክሮችና በውይይቶች እንጂ የውጭ ኃይሎች በቀየሱለት መንገድ ሊሆን እንደማይገባ ይገልጻል። መንግሥትም የውይይትና የምክክር መድረኮችን እያዘጋጀ አስቀድሞ ችግሮችን መፍታት እንዳለበት ይጠቁሟል።

ሌላው የግል አስተያየቱን የሰጠን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራተኛ ዓመት የሕግ ተማሪው ወጣት ዮሐንስ አበባው ነው። ዮሐንስ እንደሚለው ምዕራባዊያን የምስራቅ አፍሪካን ቀጣና ለመቆጣጠር ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ኢትዮጵያን እንደፈለጉ የሚያዟት አገር እንድትሆን ይፈልጋሉ ይላል። ከለውጡ በፊት ይህ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸው ነበር። የብልጽግና መንግሥት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ግን እንዲህ አይነቱን እድል አጥተዋል። የሚታዘዛቸውን መንግሥት ለማስቀመጥ ሲሉ ኢትዮጵያ ሰላም እንዳይኖራት ይጥራሉ። ኢትዮጵያ ለቀይ ባህር ቀረቤታ ያላት አገር መሆኗና የአባይ ወንዝ ምንጭ በመሆኗ አገሪቱን በመቆጣጠር በርከት ያሉ ፍላጎቶቻቸውን ማሳካት ይፈልጋሉ ይላል።

የሚታዘዛቸው መንግሥት ከሌለ ደግሞ በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ አገሪቱን ያተራምሳሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ የለውጥ ንፋስ መንፈስ ከጀመረ ጊዜ አንስቶ አንዴ የብሔር ሌላ ጊዜ የሃይማኖት ግጭቶች የሚቀሰቀሱት በውጭ ኃይሎች ነው የሚለው ዮሐንስ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያ ላይ ከሚፈጥሩት ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ተጽእኖ ባሻገር ለዘመናት በሰላምና በፍቅር የኖረው ሕዝብ እርስ በእርሱ እንዲጋጭ የተለያዩ ሴራዎችን ይዶልታሉ ይላል ዮሐንስ። በብዙ መንገድ ሞክረው እንዳሰቡት ኢትዮጵያ አልፈርስ ስትላቸው አሁን የሃይማኖት ግጭት ፈጥረዋልም ባይ ነው።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘጠና በመቶ በላይ አማኝ እንደሆነ ይነገራል የሚለው ዮሐንስ በእነርሱ አስተሳሰብ አማኝ ሕዝብ በሃይማኖቱ ከመጡበት አይደራደርም በሚል ወደ ትርምስ ሊከቱት አስበዋል ሊሆን ይችላል።

እንደ ዮሐንስ አስተያየት ሃይማኖት የጥፋትና የክፋት እጆቻችንን እንድነሰበስብ የሚያደርግ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ያቆዩዋቸውን የመቻቻልና የመተዛዘን እሴቶቻችንን አጠንክረን አብሮነታችንን በማስቀጠል የጠላቶቻችንን እቅድ ማክሸፍ ይኖርብናል።

በተለይም ወጣቶች ግጭቶች በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ አሻግረው በመመልከት በስሜት ከመጓዝ ይልቅ ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባቸዋል። ከግጭቱ ጀርባ የማን እጅ ሊኖር ይችላል? ግጭቱ ምን አይነት አገራዊ ቀውስ ሊስከትል ይችላል? ምን ኪሳራ፣ ምንስ ጥቅም ይኖረዋል? የሚለውን መመርመር እንደሚኖርባቸው መክሩን ለግሷል።

ወጣቱ ችግሮችን በመነጋገር መፍታት እንደሚቻልና መጨረሻ ላይም ቢሆን ሁኔታዎች ቦታ የሚይዙት በሀሳብ የበላይነት እንደሆነ አውቀው እጆቻቸውን ከጥፋት መሰብሰብ ይኖርባቸዋል ብሏል። ነገ አብሯቸው የሚኖረውን መከራና ችግር የሚጋራቸውን ወገናቸው ላይ ክፉ ነገር ማሰብ መልሶ የሚያሳፍር ተግባር እንደሆነ ይገልጻል።

«ሃይማኖት የግል አገር የጋራ» እንደ መሆኑ ለራሳችን ሃይማኖትና ቤተ-እምልኮ የምንሰጠውን ክብር ለሌሎች መስጠት ይጠበቅብናል ሲል ዮሐንስ የግል አስተያየቱን ሰጥቷል።

የሃይማኖት አባቶችን ተግሳጽና ምክር እንዲሁም የየሃይማኖታችንን መልካም አስተምሮ በልባችን አኑረን መልካም ሥራዎችን ብቻ በመሥራት የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ሰላም የማስጠበቅ አደራ ወጣቱ ላይ ተጥሏል ብሏል። በመሆኑም በዚሁ ልክ መስራትና ትውልዳዊ ኃላፊነትን መወጣት ከወጣቱ ይጠበቃል።

# የማዕድን ዘርፉ-ከአገራዊ ዕቅድ አምስቱ ምሶሶዎች

ስምስም መንግሥቱ

አንዱ አካባቢ ከሌላው አካባቢ መጠኑና አይነቱ ይለያይ እንደሆን እንጂ ኢትዮጵያ የእምቅ የማዕድን ሀብት ባለቤት ናት። ሀብቱ የሌለበት አካባቢ አይገኝም። ይህን እውነታ ደግሞ ከዘርፉ ተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆን፣ በየአካባቢው የሚኖረው ማህበረሰብ ጭምር በልምድ የሚያውቀውና የሚያረጋግጠው ነው። ማዕድን የማውጣቱ ሥራ ባህላዊ ነው መባሉም ማህበረሰቡ አካባቢው ላይ ያለውን ሀብት ጠንቅቆ እንደሚያውቅ አንዱ ማሳያ ነው። በተለያየ የህብረ ቀለማት ቀልብን የሚስቡት ለጣት ቀለበት፣ ለአንገት ሀብልና ለተለያየ ማስዋቢያ የሚውሉ ፈርጦች በባህላዊው የማዕድን አውጭ በቁፋሮ ከመሬት ውስጥ ወጥቶ ገበያ ላይ የዋሉ ናቸው። ባህላዊው የማዕድን ቆፋሪም ቢሆን ሽጦ ከሚያገኘው ገቢ በመጠኑም ቢሆን፣ ኑሮውን እየደጎመበት ነው።

ኢትዮጵያ ወርቅን ጨምሮ ለግንባታና ለኢንደስትሪ ግብአት እንዲሁም ለጌጣጌጥ የሚውል የሁሉም አይነት የከበሩ ማዕድናት ባለቤት ናት። ይልቁንም ተደጋግሞ የሚነሳው ይህን እምቅ ሀብቷን ለይታና በአግባቡ ባለማስተዳደር ጥቅም ላይ በማዋል በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ወደ አገር የሚገባውን የማዕድን ውጤት በአገር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለመተካትም ሆነ ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ ማድረግ አለመቻሏ ነው። ጥረቶች ቢኖሩ እንኳን አጥጋቢ በሚባል ደረጃ የሚገለጽ አይደለም። ጥሬ እቃው በአገር ውስጥ እያለ ለግንባታ ማጠናቀቂያ የሚውሉ እንደሴራሚክ፣ ለቤት ቀለምና ለተለያዩ ፋብሪካዎች ግብአት የሚውሉ በውጭ ምንዛሪ ከውጭ ተገዝተው እንደሚገቡ ተሞክሮዎች ያሳያሉ። ዘርፉ በክትትልና ቁጥጥር ማነስም ለህገ ወጥነት መጋለጡ ይታወቃል። በዚህ የህገ ወጥ ሥራ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ የአገርን ጥቅም በማስቀረት የሚፈጥሩት ተጽዕኖም በግልጽ ይታያል።

ዘርፉን ለማልማት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይና ቴክኖሎጂ የሚፈልግ እንደሆነ ከዘርፉ ባለሙያዎች እንሰማለን። ሀብቱ እያለ በአቅም ውስንነት በሚፈለገው ልክ መጠቀም አልተቻለም። ዘርፉ በተለያየ ተግዳሮት ውስጥም ሆኖ እንደአገር ከቀጠናው አገራት ጋር በልማት ለመተሳሰር የተነደፈው የአስር አመት መሪ ዕቅድ ውስጥ አንዱ የኢኮኖሚው ማሳደጊያ የጀርባ አጥንት ተደርጎ በእቅዱ ተካትቷል። የእቅዱ አካል ሆኖ ውጤት እንዲያመጣ ወይንም አስተዋጽኦ እንዲኖረው ካስፈለገ መንግሥት ብቻ ሳይሆን በዘርፉ ላይ በተለያየ መንገድ ድርሻ ያላቸው ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድም በምርምርና ጥናት እንዲሁም በሀሳብ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይጠቀሳሉ። በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ዩኒቨርሲቲዎች ተደራሽ ሆነዋል። ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን በአካባቢው ስላለው የማዕድን ሀብት በአይነት፣ በመጠንና ሊያስገኙ ስለሚችሉት ጥቅም ጭምር በጥናትና ምርምር ለይቶ ዘርፉን ለሚመራው አካል የጥናት ውጤታቸውን እንዲያውቁት ማድረግ፣ ግንዛቤ በመፍጠርም ከፍ ያለ ሚና ይጠበቅባቸዋል። ብዙዎች በዚህ መልኩ እንደሚንቀሳቀሱ ቢታወቅም በሚያጋጥማቸው የጥናትና ምርምር የበጀት እጥረት፣ ዘርፉን ከሚመራው አካል ጋር ተናብቦ ባለመስራት፣በትኩረት ማነስና በተለያየ ምክንያት ሥራዎች እንዳልተሰሩም ሀሳብ ይነሳል። በዚህ ረገድ በአገሪቱ አንጋፋ ከሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነውን ጅማ ዩኒቨርሲቲን በማዕድን ዘርፉ በጥናትና ምርምር እያበረከተ ስላለው አስተዋጽኦና እንደአገር ስለተያዘው አገራዊ የዕቅድ አቅጣጫ ዘርፉ ስለሚኖረው ሚና በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሥር ከሚገኘው ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሲቪልና አካባቢ ምህንድስና ትምህርት ክፍል ዲንና መምህር ከሆኑት ማሙዬ ሁሴን ጋር ቆይታ አድርገናል። መምህር ማሙዬ በሲቪል ኢንጂነሪንግና ኃይድሮ ፓወር ትምህርት የተማሩ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜም የአንደኛና የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማስተማርና በምርምር በማገዝ በዩኒቨርሲቲው በማገልገል ላይ ናቸው።

**በአገር ደረጃ የአስር አመት ዕቅድ በመንደፍና ከዛም ሳቅ ብሎ ለሚቀጥሉት 30 አመታት በግብርና፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም ኢንደስትሪ በሁሉም አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ልማትን በማፋጠን ኢኮኖሚን ለማሳደግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። በእቅድ አቅጣጫው ትኩረት ከተሰጣቸው ከአምስቱ ምሶሶዎች(ፒላር) ተለይተው በአገራዊ ልማት ዕቅዱ ከተያዙት መካከል አንዱ የማዕድን ዘርፍ ነው። ትኩረት መሰጠቱ ተገቢ ነው**

መምህር ማሙዬ እንዳሉት በአገር ደረጃ የአስር አመት ዕቅድ በመንደፍና ከዛም ላቅ ብሎ ለሚቀጥሉት 30 አመታት በግብርና፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም ኢንደስትሪ በሁሉም አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ልማትን በማፋጠን ኢኮኖሚን ለማሳደግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። በእቅድ አቅጣጫው ትኩረት ከተሰጣቸው ከአምስቱ ምሶሶዎች(ፒላር)ተለይተው በአገራዊ ልማት ዕቅዱ ከተያዙት መካከል አንዱ የማዕድን ዘርፍ ነው። ትኩረት መሰጠቱ ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ መልክአ ምድሯ(ቶፖግራፊዋ) የተለያየ ሲሆን፣ ይህም በተራራማ፣ ሜዳማና ዝቅተኛ ይገለጻል። በተለያየ ጊዜ በተካሄደ ተፈጥሯዊ የመሬት እንቅስቃሴም እሳተ ጎመራ(ቮልካኖ) ያለበት አካባቢዎችም አሏት። እጅግ በጣም ጥንታዊ የሆኑ አለቶች(ሮኮች) መገኛም ናት። በረጅም ጊዜ የመሬት እንቅስቃሴ (ሴግመንቴሽን) አፈር ሲከማችና ክምችቱም በሺዎች አመት ሲቆጠር አካባቢው ላይ የሀብት ክምችት እንዲኖር ያስችላል። ኢትዮጵያ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ስኩዌር ሜትር አካባቢ የሚገመት ስፋት ያላት ትልቅ ሀገር ናት። የመሬት ስፋቷም ከአፍሪካ ጋር ሲነጻፀር ሽፋኑ አራት በመቶ ያህል ብልጫ እንዳለው መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ሁሉ መረጃ ኢትዮጵያ ሰፊ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት እንዳላት ያሳያል። የተፈጥሮ ሀብቱ ሰፊ ከመሆኑ አኳያ መንግሥት በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ከዘርፉ ለመጠቀም የተያዘው አቅጣጫ ተገቢነት አለው።

እስካሁን ባለው ክንውን ዘርፉ ላይ የተሰሩትን ሥራዎች መምህር ማሙዬ እንዲህ ያስረዳሉ፤ፖሊሲዎን በማዘጋጀትና ባለሀብቱን በመሳብ እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም፤ አንዳንድ ማዕድናትን ጥቅም ላይ በማዋል አገራዊ የኢኮኖሚ ጥቅም እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር ብዙ ሥራዎች ይጠበቃሉ። ሥራው እየተከናወነ ያለው በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ በጥቂት የሰው ኃይል ነው። ይህ ደግሞ ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ጥቅም ሳያስገኝ ቀርቷል። ይህን ለማሻሻል በመንግሥት በኩል በተለይም በማዕድን ሚኒስቴር በኩል ዘርፉን ለማዘመን የሚያግዝ ፖሊሲ ከማሻሻል ጀምሮ እየተወሰደ ያለው እርምጃ አበረታች ነው። ትምህርት ተቋማት በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች በሚችሉት ሁሉ ትብብር በማድረግ ተደራሽ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሲባል ግን የበለጠ መስራት ይጠበቃል ከሚል እንጂ በትምህርት ተቋማት አማካኝነት ተስፋ ሰጭ የሆኑ የምርምር ሥራዎች ተከናውነዋል። የምርምር ውጤቶቹ ከኢኮኖሚ አንጻር ያበረከቱት አስተዋጽኦ፣ ወደፊትስ ምን ቢደረግ ምን ማግኘት ይቻላል፣ ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ እንዲችል ምን አይነት ድጋፍ መደረግ አለበት የሚል የጥናትና ምርምር ሥራዎችም ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርትን የሚመራው እንዲሁ ትኩረት በመስጠት ትምህርት ሚኒስቴርና የማዕድን ምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ለይቷል። በፖሊሲ ደረጃም አዘጋጅቷል። ይህም ለማዕድን ዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል። አገራዊ የማዕድን ጥናት ምርምርና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ቦታዎች መለየት በሚል ጥናት እንዲካሄድ የተለያዩ ቡድኖችን በማቋቋም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ማዕድኖች ከመሬት ውስጥ በቁፋሮ በሚወጡበት ጊዜም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሲባል ማዕድኑ የወጣበት አካባቢ እንዴት መልማት እንዳለበት እንዳይዘነጋ ነው። ምክንያቱም ማዕድኑ ጥቅም እንዳስገኘው ሁሉ ጉዳትም ማስከተል የለበትም። በመሆኑም የምርምርና ጥናት ሥራው ሁለገብ ነው መሆን ያለበት።

ጅማ ዩኒቨርሲቲም እንዲህ ያሉ ተሞክሮዎች እንዲበረታቱ ነው የሚያደርገው። በዩኒቨርሲቲው የማቴሪያል ሳይንስ ኤንድ ኢንጂነሪንግ ፋካልቲ(ትምህርት ክፍል)፤ ውስጥ የሚያስተምሩ አንዳንድ መምህራን ጥናት በማካሄድ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። ለአብነትም ጅማ ከተማ ከፍተኛ የሆነ የሸክላ አፈር (ክሌይ) ክምችት ይገኛል። የሸክላ አፈር በውስጡ የተለያዩ ማዕድናት(ሚኒራል) ይገኛል። ይህ የማዕድን ሀብት ለግንባታ ለሚውል ለጡብ ምርት ግብአት ከመዋል በተጨማሪ ለምን አገልግሎት ሊውል እንደሚችልና የሀብት መጠኑን ወይንም ክምችቱን ለማወቅ ነው በዩኒቨርሲቲው መምህራን ጥናት እየተደረገ ያለው።

በጅማ ዞን ውስጥ በማዕድን የሀብት ክምችት ደረጃ ከሚጠቀሰው አንዱ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ነው። ያለው የክምችት መጠን አገሪቱ ለሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች የሚያስፈልጋትን ግብአት ማሟላት የሚያስችል ሲሆን፣ ሀብቱ ከጅማ ከተማ በ44ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። በአካባቢው መኖሩ ከአስር አመት በፊት የሚታወቅና ለአካባቢው ነዋሪዎችም ከፍተኛ የሥራ ዕድል በመፍጠር አስተዋጽኦ አበርክቷል። አሁን ላይ ግን የሚገኝበት ደረጃ ለጊዜው መረጃው እንደሌላቸው የሚገልጹት መምህር ማሙዬ በተመሳሳይ ከጅማ ከተማ 180ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ጊቤ ተብሎ በሚጠራው አካባቢም ሀብቱ እንደሚገኝ መረጃዎች እንደሚጠቁሙ ተናግረዋል። እንደርሳቸው ማብራሪያ በቅርቡ ከደቡብ ክልል ሥር ወጥቶ የተደራጀው በደቡብ ምዕራብ ክልል ውስጥ ቦንጋ፣ ዳውሮ፣ በተባሉ አካባቢዎች ከፍተኛ የድንጋይ ከሰል ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። አካባቢዎቹ ለጅማ ዞን በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛሉ። የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪ ምሁራንም በሥፍራው ተገኝተው ከአካባቢው አርሶ አደሮች ባገኙት መረጃና እነርሱም እንዳረጋገጡት አርሶ አደሮቹ የአካባቢውን አፈር በባህላዊ መንገድ በማቅለጥ ብረት ይሰራሉ። የዚህ ውጤት የሚያመላክተው በአፈር ውስጥ ከፍተኛ ክምችት ያለው ማዕድን(አይረን) መኖሩን ነው። ብረት(ሜታል) ሚኒራል ወይንም ማዕድን ከሚባለው ውስጥ ነው የሚገኘው። በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች በማዕድን የበለፀገ ማዕድን አለ ብሎ በሙሉ እምነት መናገር ይቻላል። ትኩረት በማድረግ የብረት ማዕድንን በብዛት መጠቀም ይገባል።

የማዕድን ዘርፉን በማልማት በአገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው አቅዶ መንቀሳቀስ ለመንግሥት ብቻ የተተወ ተግባር እንዳልሆነ የጅማ ዩኒቨርሲቲን ተሞክሮ መውሰድ ይቻላል። መምህር ማሙዬ እንደገለጹት ዩኒቨርሲቲው ኃላፊነት አለብኝ በሚል መንፈስ ማዕድንን ጨምሮ በተለያየ ዘርፍ የአስር አመት ስትራቴጂ እቅድ ነድፏል። ዕቅዱንም በትምህርት ሚኒስቴር አፀድቆ ነው ወደ ሥራ የገባው። ዩኒቨርሲቲው የአካባቢውን የማዕድን ሀብት ክምችት ባለው አቅም የመለየት ሥራ ለመሥራት ጥረት ያደርጋል። አቅም ካነሰው ደግሞ ለዘርፉ ምርምር ሥራ የሚያግዝ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይና በማዕድን ሚኒስቴር ሥር ብዙ ቤተሙከራዎች ይኖራሉ የሚል እምነት አላቸው መምህር ማሙዬ። ናሙናዎችን በመውሰድ በነዚህ ተቋማት መጠቀም የሚቻልበት ዕድል በመኖሩ ተግዳሮት እንደማይሆን ያምናሉ። ዩኒቨርሲቲው በማዕድን ዘርፍ የተለየ የትምህርት ክፍል ባይኖረውም የአገር ዕቅድን ለመጋራት የሚያግደው ነገር እንደሌለ ይገልጻሉ። እንደአገር ያለውን እምቅ ሀብት ለመጠቀምና አገራዊ ዕቅድንም ከግብ ለማድረስ ዩኒቨርሲቲው በሚችለው ሁሉ ያደርጋል ብለዋል። በግላቸው የማዕድን ሚኒስቴርን ድረ ገጽ ለመጎብኘት ባደረጉት ጥረትም አዳዲስ የማዕድን አይነቶችን የማስተዋወቅና ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚደረገው ጥረት አበረታች ሆኖ አግኝተውታል። በመገናኛ ብዙሃንና በተለያየ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴ የበለጠ በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይገባል ይላሉ መምህር ማሙዬ። በዘርፉ የሚያስፈልጉ ከፍ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም እንዲቻል ደግሞ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች በተለያየ አገር በተወከሉ አምባሳደሮች አማካኝነት በመሳብ መጠቀም እንደሚገባም ሀሳብ ሰጥተዋል። አንድ በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልግ ባለሀብት ምን ማሟላት እንዳለበት የሚያሰራ ህግ በአገር ደረጃ በመኖሩ የሚጠበቀው ህጉን መሬት ማውረድ ወይንም መተግበር ሲሉም አክለዋል።

መምህር ማሙዬ በሰጡት ምክረ ሀሳብ የማዕድን ዘርፉ የግጭት መንስኤ የሚሆንበት አጋጣሚ መኖሩን ሀብቱ ካላቸው አገሮች ተሞክሮ መውሰድ እንደሚቻል ጠቁመዋል። እንደርሳቸው ሀሳብ የማዕድን ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታና መጠን ለማወቅ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውል ለመለየትና ለኢኮኖሚ ግንባታም ሊኖረው ስለሚችለው አስተዋጽኦ፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትም ስላለው አበርክቶ በምርምር ለመለየት ጥረት እንደሚደረገው ሁሉ ሀብቱ የግጭት መንስኤ ሳይሆን እንዴት ለአገር ብልጽግና ይጠቅማል። እንዴት ሰላማዊ መንገድ ያመጣሉ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ከዘርፉ ምን ይጠቀማል፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ለአደጋ ሳይጋለጡ እንዴት ሥራቸውን መሥራት እንደሚችሉ ለይቶ መሥራት እንደሚጠበቅ አስገንዝበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የትዝታ ድሮች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከእናቱ ጋር ጎን ለጎን ቁጭ ብሏል። እድሜ ድሩን አድርቶባቸው እናቱን ወደ እርጅና እሱን ደግሞ ወደ ጉልምስና ወስዷቸዋል። የእናቱ አዛውንት እጅ እንደ ልጅነት ጊዜው ከበራ ጭንቅላቱ ላይ ሊወጣ ሲታከከው ይታየዋል።

‹አይ እማ! ዛሬም ድረስ እጆችሽ ይፈልጉኛል› አለ ደስ ባለው ፊት ወደ እናቱ እያየ።

‹እናት አይደለሁ፤ እንዴት አልፈልግህም! የእናት እናትነት የሚያበቃው ስትሞት ብቻ ነው..። በሕይወት እስካለሁ ድረስ ሁሌም ትንሽ ልጄ ነህ› አሉት።

‹ያኔ ጸጉሬን ነበር ዛሬ ምኔን ትዳብሺዋለሽ ራሰ በራ ነኝ..› አለ በራውን በእጁ እያሻሻ።

‹እናት ለልጇ የፍቅር ቦታ አታጣም። በራህም ቢሆን ለእጆቼ የብዙ ፍቅር መገኛዎች ናቸው› አሉት ከቡናው ፉት እያሉ።

‹ዛሬ ላይ ለኔ ራሰ በራ መሆን ያንቺ እጆች ያሉበት ይመስለኛል። ለአስራ ስምንት አመት ያህል እጅሽ ከራሴ ላይ አልወረደም ነበር። ሲል በኃይል ሳቀ። ሳቁ እናቱንም አስቋቸው አብረው ሳቁ።

ከሳቁ መልስ መቆሚያ አላገኘም፤ እናቱን አጠገቡ አስቀምጦ ወደ ልጅነት ዘመኑ በሀሳብ መነነ። ምናኔው ውስጥ በልጅነት ገዳሙ ውስጥ የልጅነት ጻዳሎቹን ካባ ለብሰው አገኛቸው። ምናኔው ውስጥ የማለዳ ድርሳኖቹን ጤዛ ለብሰው አትሮኖስ ላይ አገኛቸው። ምናኔው ውስጥ የጠዋት ተንስአውን በልጅነቱ አጥቢያ ውስጥ አገኛቸው። ምናኔው ውስጥ ባለቀለም ቡረቃውን ዘመን ለብሰው አገኛቸው።

ልጅነቱ የሕይወት ታሪኩ ነው። ሲሞትም ሆነ ሲኖር እንዲወራለት የሚፈልገው ያ የጠዋት ገድሉ ነው። ከአምና በቀር ለማንም የሚነግረው ሌላ ታሪክ የለውም። ከእናቱ ጋር አልቦና ክርን፣ መስቀልና አንገት ነበር።

የእናቱ ድምጽ ያን ሁሉ የዘመን ገደል ማሚቱ፣ ያን ሁሉ የዘመን ጥቀርሻ አልፎ ዛሬም ድረስ ይሰመዋል። ድምጽዋ የሚጎላበት ከእሷ በቀር ማንም ጠርቶት በማያውቀው የብቻ ስሟ ስትጠራው ነው። ‹ጌታዬ ነው› የምትለው..። ስሙ ይስሀቅ ሆኖ ሳለ ጌታዬ ብላ ነው የምትጠራው። ለምን ጌታዬ እንደምትለው አንድም ቀን አስቦት፣ አንድም ቀን ነግራው አታውቅም። በቃ ጌታዬ ትለዋለች።

ያ ጥሪ፣ ያ እናትነት ተመልሶ በአንድ ጎጆ ውስጥ ዳግሞ ቢበቅል ይላል። አሁንም ከእናቱ በቀር ማንም ጌታዬ የሚለው የለም። በይስሀቅ ውስጥ የበቀለውን ያን ሁሉ ተጽዕኖ ችላ ዛሬም ድረስ ጌታዬ ነው የምትለው። ዓለም ብዙ ሆኖ ይስሀቅ ይለዋል፤ እናቱ አንድ ሆና ጌታዬ ትለዋለች። ከዛ ሁሉ እልፍና ከዛች አንዷት ድምጽ መሀል የእናቱ ድምጽ ብቻ ነው የሚሰማው።

ከምናኔው ውስጥ ሌላም የትዝታ ሰበዝ መዘዘ። በልጅነቱ የእናቱ እጅ ካናቱ ላይ ወርዶ አያውቅም ነበር። አጠገቧ ካለ እጇ አናቱ ላይ ነው መገኛው። ታሻሽዋለች፣ ትዳብሰዋለች፣ ያልበላውን ታክለታለች። የጭንቅላቱን ግርጌና ራስጌ በጣቶቿ ትሄድበታለች። በጣቶቿ አናቱን እየቆፈረች ተባይ ይሁን ሌላ ነገር ትፈልጋለች።

አንዳንድ ጊዜ ጭኗ ላይ ደገፍ ታደርገውና፣ ጉያዋ ውስጥ ወሸቅ ታደርገውና፣ ክንዷ ላይ ጋደም ታደርገውና፣ ደረቷ ላይ ጣል ታደርገውና ትደባብሰዋለች። የእናቱ እጆች አይረሱትም..ታሞ፣ ተከፍቶ ዳብሰው ፈውሰውት ያውቃሉ። ርቦት፣ ጠምቶት አርከተውት ያውቃሉ። አዝኖ፣ ተክዞ አጽናንተውት ያውቃሉ። ታርዞ፣ ተራቁቶ አልብሰውት ያውቃሉ።

የእናቱ እጆች እንደ እግዜር እጆች ሰዎች ያላወቋቸው እሱ ብቻ ተዳብሶ የዳነባቸው መለኮታዊ ይመስሉታል። የእናቱ ጣቶች ባህር የሚከፍሉ በትረ ሙሴ ሆነው እልፍ ቀን ታዝቧቸው ያውቃል። ብዙ ጊዜ ተገርሞና ተደንቆ እጆቿን በተለይም ጣቶቿን ወደ አይኑ አቅርቦ አስተውሏቸው ያውቃል። ብዙ ጊዜ ያልደረሰበት የተሸሸገ ሚስጢር ካለው ብሎ የመዳፏን መስመሮች፣ የጣቶቿን አፈጣጠር ታዝቦት ያውቃል፤ ግን አዲስ ነገር አላገኘባቸውም ፤ግን ይፈውሱታል፤ ያጽናኑታል።

የእናቱ ጉያ የጽድቅ መንገዱ ነው፤ ቡና ስታፈላ ወይም ደግሞ ሰው ቤት ቡና ተጠርታ ስትሄድ ጉያዋ ውስጥ አይጠፋም። የልጅነቱ ብዙ ጊዜ በእናቱ ጉያ ውስጥ ያለፈ ነው። ጉያዋ ውስጥ ዛሬም ድረስ ያልደረሰበት አንዳች የጸጋና የበረከት መና አለው። አድጎ የሚያላምጠው፣ ጎልምሶ የሚያመነዥከው የሕይወት እንጀራ። በሕይወት ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚመጡ የተፈጥሮ ጸጋዎች እንዳሉ ዛሬ ነው

የሰው ልክ ከዛሬ ካልሸሸ፣ ከአሁን ፈቀቅ ካላለ የትዝታ ሙጀሌ አይበላውም። ዛሬ ትላንት ሲሆን ሁሉም ትዝታ እንደሆነ የገባን ጥቂቶች ነን። ትላንት ላይ ሆኖ ያ የልጅነት ጊዜው እንዲህ እንደሚናፍቀው ቢያውቅ መጽናኛ ያስቀር ነበር። የሚፈጀን የሕይወት ረመጥ በዛሬና በትላንት መካከል ያነደድነው እቶን ነው። የምናከው የትላንትን እከክ ነው። ዛሬ እከክ የለውም። ወደ ነገ እንጂ ወደ ትላንት የሚሮጥ የተፈጥሮ ህግ የለንም፤ ትተንው ወደመጣንው አምና የምንመለሰው እንዲህ ባለው የትዝታ ረመጥ ነው።

አድጎ እንኳን የእናቱ እየሱሳዊ ጣቶች ይናፍቁታል። አድጎ እንኳን የእናቱ ጉያ ይመጣበታል። ዛሬ ላይ ያልሄደበት፣ ያላየው ውድና ቅንጡ ሕይወት የለም። የሰላምና የደስታ ስፍራ ወደተባለ ዓለማዊ ቦታ ተዝናንቶና ውድ ገንዘብ ከፍሎ ያውቃል።

እንደ እናቱ ጉያ ምቹና ሰላም ያለው ስፍራ ግን አላገኘም። ከሁሉም በኋላ ተመልሶ ልጅ መሆን ያምረዋል። ከሁሉም በኋላ ተመልሶ በእናቱ ማህጸን ውስጥ መብቀል ያምረዋል። ከሁሉም በኋላ በእናቱ ተምጦ መወለድ ከዛም ጌታዬ ብላ ስትጠራው የነበረው ልጅነታዊ ዓለም ያምረዋል። ምድር ላይ አንድ እድል አግኝቶ ወደኋላ የመመለስ ስልጣን ቢያገኝ ልጅ ሆኖ ራሱን እናቱ ጉያ ውስጥ ይፈጥረው ነበር። የልጆቹ ልጅነት ያስቀናዋል። በየጎዳናው የሚያያቸው ልጆች ልጅነት ያስቀናዋል።

ከሀሳቡ መልስ እናቱን ያገኛት ሶፋው ላይ እንቅልፍ ጥሏት ነበር። ባንቀላፋችበት በደንብ አያት፤ ነጭ ሽበቷ የሻሿን ድንበር ጥሶ ግንባሯ ላይ አፎልቋል። ለእሱ ኖረው ለእሱ ያረጁት እጆቿን፣ እሱን በማቀፍ የሰለሉት ክንዶቿን፣ እሱን በመዳበስ የጃጁት ጣቶቿን፣ እሱን በማየት ኖረው የሞጨሞጨት አይኖቿን አስተዋላቸው።

ለዚህ ሁሉ የሚሆን ምን ውለታ አለው? ምንም። እንደልጅነት ጊዜው አዛውንት ክንዷን ተንተርሶ አጠገቧ ጋደም አለ። እሱ ሲያንቀላፋ እሷ ነቅታ ነበር። ልጇን ክንዷ ላይ፣ እቅፏ ውስጥ ስታገኘው የተሰማት ደስታ እንደ ጥንቱ ነበር። በተኛበት አዛውንት እጇን ልካ መላጣ ራሱ ላይ አሳረፈችው..እንደልጅነቱ ልትዳብሰው።

# ዓለም አቀፍ



## ኢራን ስዊድናዊውን ዶክተር በሞት ለመቅጣት መዘጋጀቷ እንዳሳሰባት ስዊድን ገለጸች

ኢራንን ሲሰልል ነበር የተባለው የኢራን የዘር ሃረግ ያለው ስዊድናዊ ዶክተር የተላለፈበት የሞት ቅጣት በዚህ ወር እንደሚተገበር መሰማቱ ስዊድንን "እጅግ እንዳስጨነቀ" የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገለጹ።

የ50 ዓመቱ የሕክምና ባለሙያ ከ15 ቀናት በኋላ (ግንቦት 13/2014 ዓ.ም) እንደሚገደል ምንጮች ተናግረዋል። የውጭ ጉዳይ ሚንስትሯ አን ሊንዴ በትዊተር ገጻቸው፣ አገራቸው ስዊድን እና የአውሮፓ ኅብረት የሞት ቅጣቱን እንደሚያወግዙት የገለጹ ሲሆን እንዲለቀቅም ጠይቀዋል። አሕመድሬዛ ጀላሊ የተባለው የድንገተኛ ሕክምና ባለሙያ የሆነው ግለሰብ እንደ አውሮፓውያኑ በ2016 ወደ ኢራን ለሥራ በተጓዘበት ወቅት ለእስራኤል ይሰልላል በሚል በቁጥጥር ስር ውሏል።

የአገሪቱ አብዮታዊ ፍርድ ቤት በ2017 የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ያልተገባ የፍርድ ሂደት ባሉት ችሎት የሞት ቅጣት በይኖበታል። ጀሊል "ወንጀሉን" እንዲያም ጫን እንደተደረገበት እና ያ ካልሆነ በስዊድን የሚገኙት ልጆቹ ላይ ጉዳት እንደሚደርስባቸው እንደተናገረ ተገልጿል።

ከአውሮፓ ኅብረት ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ተጠቅሞ ለኢራን እንዲሰልል የተጠየቀው ጀሊል ለኢራን እንዲሰልል ተጠይቆ አሻፈረኝ በማለቱ ለብቻው እንዲታሰር ሳይደረግ እንዳልቀረም ተነግሯል። በፈረንጆቹ 2020 ግለሰቡ የሞት ቅጣቱ ሊፈጸም እንደሆነ ተነግሮት ነበር። ሆኖም ቅጣቱ ሳይፈጸም ወራት ተቆጥረዋል።

ትላንትና የስዊድን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መረጃ ካላቸው ሰዎች ሰማሁ ብለው እንደተናሩት ከሆነ የጀሊል የሞት ቅጣት በኢራን የዘመን አቆጣጠር በተያዘው ወር መጨረሻ የሚፈጸም ይሆናል። የኢራን ፍርድ ቤትም የአገሪቱ ብሔራዊ ሚዲያም ስለ ጉዳዩ ያሉት ነገር የለም።

ይህ የኢራን እርምጃ በስዊድን ፍርድ ቤት በቀድሞ የኢራን የፍርድ ቤት ባለሥልጣን ሃምቢ ኑሪ ላይ ከተላለፈበት ውሳኔ ጋር ግንኙነት እንዳለውም ተገምቷል። ሃምቢ ኑሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2019 በስቶኮልም አየር ማረፊያ በቁጥጥር ስር ውሏል። በአውሮፓውያኑ 1988 በኢራን በፖለቲካ እስረኞች ላይ በተፈጸመው የጅምላ ግድያ አለው በተባለው ተሳትፎ ክስ መስርቶበታል።

ሆኖም ተከሳሹ ድርጊቱን ክዶ የተከራከረ ሲሆን የተሳሳተ ሰው ይዛችኋል እንዳለም ተሰምቷል። የፍርድ ሂደቱ ትላንት የተጠናቀቀ ሲሆን የመጨረሻ ውሳኔ በሐምሌ ወር እንደሚሰጥ ይጠበቃል። ግለሰቡ የዕድሜ ልክ እስራት ሊጠብቀው እንደሚችልም ተገምቷል። ይህ ከተሰማ በኋላ የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለስዊዲን አቻቸው ደውለው ሕገ ወጥ ካሉት እስር ኑሪ እንዲፈታ መጠየቃቸውን የኢራን ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ዘግቧል።




## በህንድ በቡድን ተደፍራ ሪፖርት ልታደርግ የሄደችውን ታዳጊ ፖሊስ ደፍሯል መባሉ ቁጣ አስነሳ

በህንድ ኡታር ፕራዴሽ ግዛት በቡድን የተደፈረች አንዲት የ13 ዓመት ታዳጊ ሪፖርት ልታደርግ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በሄደችበት ወቅት በፖሊስ ተደፍራለች መባሉ ቁጣን ቀስቅሷል።

በፖሊሱ ላይ የወንጀል ክስ የተከፈተበት ሲሆን ከስራ መታገዱን አንድ ከፍተኛ የፖሊስ ባለስልጣን ተናግረዋል። ታዳጊዋ ባለፈው ወር በአራት ሰዎች በቡድን መደፈሯን የተናገረች ሲሆን አክሎም የታዳጊዋ በፖሊስ ተደፍራለች መባሉ ከፍተኛ ቁጣን አስከትሏል። የልጅቷ አባት ለፖሊስ ባቀረቡት አቤቱታ አራት ወንዶች ልጅቷን አጎራባች ወደሆነችው ማድያ ፕራዴሽ ግዛት ወስደው ለአራት ቀናት ያህል በቡድን እንደደፈሯት አስረድተዋል። ግለሰቦቹ ወደ መንደሯ መልሰው ካመጧት በኋላ ሸሽተዋል ተብሏል።

በማግስቱ ታዳጊዋ ሪፖርት ለማድረግ ከአክስቷ ጋር ወደ አቅራቢያዋ ፖሊስ ጣቢያ የሄደች ሲሆን በስፍራው የነበረው ፖሊስ እንደደፈራትም ኤንዲቲቪ የዜና ጣቢያ ዘግቧል። የላሊትፑር ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ኒኪል ፓታክ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት ቻይልድ ላይን በተሰኘ በጎ አድራጎት ድርጅት ወደ ቢሯቸው እንደመጣችና የተፈጠረውን ክስተት በነገረቻቸው ወቅት "ወዲያውኑ ክስ መመስረቱን አረጋግጫለሁ" ብለዋል።

ዜናው በህንዳውያን ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን የፈጠረ ሲሆን በርካቶች ህግና ስርዓትን በተመለከተ ጥያቄ እያነሱ ይገኛል። የኮንግረስ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ፕሪያንካ ጋንዲ ቫድራ በሂንዲ ቋንቋ ባሰፈሩት የትዊተር መልዕክት "የፖሊስ ጣቢያዎች ለሴቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ካልሆነ ታዲያ ቅሬታ ለማቅረብ የት ይሄዳሉ?" ሲሉ ጠይቀዋል።

"መንግሥት የሴቶችን ቁጥር በፖሊስ ጣቢያዎች እንዲጨምር፣ የፖሊስ ጣቢያዎች ለሴቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ምን ያህል እያሰበበት ነው" ሲሉ አክለዋል። በህንድ ዋና ከተማ ደልሂ አንዲት ወጣት በአሰቃቂ ሁኔታ በቡድን ተደፍራ ሕይወቷ ካለፈችበት ከአውሮፓውያኑ 2012 ጀምሮ መደፈር እና ፆታዊ ጥቃቶች ከፍተኛ ትኩረት አግኝተዋል።

# ስፖርት





## የምስራቅ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮና በኢትዮጵያ እየተካሄደ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

ከኦሊምፒክ ስፖርቶች መካከል አንዱ የሆነው ጠረጴዛ ቴኒስ እአአ ከ1988 በታላቁ መድረክ ውድድር እየተደረገበት ይገኛል። በዚህ ስፖርት እንደ ቻይና ያሉ አገራት በውጤታማነት ተጽእኖ ፈጣሪዎች ሲሆኑ፤ በአንጻሩ በአፍሪካ የናይጄሪያ እና የሰሜን አፍሪካ አገራት የበላይነቱን ይይዛሉ። የጠረጴዛ ቴኒስ ስፖርት በኢትዮጵያ እንደ መዝናኛ ተዘውታሪ ከሆኑ ስፖርቶች አንዱ ቢሆንም ትልቅ ትኩረት ባለማግኘታቸው በውጤታማነት መራመድ ካልቻሉ ስፖርቶች መካከልም ይጠቀሳል።

ፈጣን እንቅስቃሴና ቅልጥፍናን የሚጠይቀው ይህ ስፖርት በተለይ በታዳጊ እና ወጣቶች በስፋት ይዘወተራል፤ ስፖርቱ ለአእምሯዊም ሆነ አካላዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ባለሙያዎች ያረጋግጣሉ። ይሁንና ከግማሽ በላይ የሚሆነው ህዝቧ ወጣት በሆነው ኢትዮጵያ በስፖርቱ ተጠቃሚ መሆንም ሆነ በትልቅ ደረጃ ስኬታማ ለመሆን አልቻለችም። ነገር ግን በጥቂት ክለቦችና በግለሰቦች የግል ጥረት በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ ተወዳዳሪ ከሆኑ አገራት ተርታ ኢትዮጵያም ልትሰለፍ ችላለች።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽኖች አባል ከሆነችባቸውና ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ ስፖርተኞች መካከል አንዱ የጠረጴዛ ቴኒስ ሲሆን፣ የዓለም አቀፉ ጠረጴዛ ቴኒስ አባል የሆነችው 1964 ዓ.ም መሆኑ ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። እአአ በ2013 የምስራቅ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ማህበር ሲቋቋምም ከመስራቾቹ መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች።



ኢትዮጵያ በቀጣናው መልካም የሚባል እንቅስቃሴ እና ተቀባይነት ያላት አገር በመሆኗም የምስራቅ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮናን ለማዘጋጀት በቅታለች። ኢትዮጵያ ከ28 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ቻምፒዮና ታዘጋጃለች፤ ይኸውም ለአገር ገጽታ ግንባታ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል። ከዓመታት በኋላ ለሚደረገው ለዚህ ውድድር ሲደረግ የቆየው ቅድመ ዝግጅት ተጠናቆም ቻምፒዮናው ትናንት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መጀመሩን የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታውቋል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ባዘጋጀችው ቻምፒዮና ሜዳሊያ ውስጥ መግባት መቻሏ ይታወሳል። በውድድሩ ትልቁን ውጤት ያስመዘገበችውም ዩጋንዳ እአአ በ2019 ባስተናገደችው ውድድር ነበር። በወቅቱም አንድ የወርቅ እና ሁለት የነሃስ ሜዳሊያ መገኘቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የምስራቅ አፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን በስሩ 14 አገራትን ያቀፈ ቢሆንም በውድድሩ ላይ ተሳታፊ እየሆኑ የሚገኙት ስምንት አገራት መሆናቸውም ታውቋል። እነርሱም ኢትዮጵያን ጨምሮ ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ኮሞሮስ፣ ሲሼልስ፣ ሞሪሺየስ፣ ሩዋንዳ እና ዩጋንዳ ናቸው። ውድድሩ በነጠላና በቡድን የሚደረግ ሲሆን፤ የውድድሩ ተሳታፊ አገራት በወንድና በሴት እስከ አምስት አትሌቶች የማሳተፍ እድል አላቸው። ኢትዮጵያ በበኩሏ የውድድሩ አዘጋጅ አገር በመሆኗ ተጨማሪ ተወዳዳሪዎችን የማሳተፍ እድል ይኖራታል። በዚህም መሰረት 10 ወንድና 10 ሴት ተጫዋቾች ዝግጅት አድርገው በውድድሩ ላይ እየተካፈሉ እንደሚገኙ ታውቋል።

ውድድሩ ከሚያዚያ 27 እስከ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ለሶስት ቀናት የሚደረግ ይሆናል። ይህ ውድድር ለአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮና እንደ ማጣሪያ የሚያገለግል ውድድር ሲሆን፤ በመጪው ዓመት ጥቅምት ወር በአልጄሪያዋ አልጀርስ በሚካሄደው ቻምፒዮና በነጠላ ከ1 እስከ 8 ባለው ደረጃ ውድድራቸውን የሚያጠናቅቁ እንዲሁም ሁለት ቡድኖች ተካፋይ እንደሚሆኑ ታውቋል። በዚህ ውድድር የተሻሉት ደግሞ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በሚካሄደው የዓለም ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮና አፍሪካን ወክለው ይወዳደራሉ።

ውድድሩን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን ከተቻለም በቀጣይ የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ውድድሮች ለማዘጋጀት እድል እንደሚፈጥር የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ተስፋዬ ብዛኔ ገልጸዋል። ቻምፒዮናው በኢትዮጵያ መካሄዱ አገሪቱ የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ እንዲሁም ለቱሪዝምና ለሆቴሎች ጥሩ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ፕሬዚዳንቱ አክለው ገልፀዋል።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውም ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም:- SinoCellTech Ltd.<br>የአመልካች አድራሻ:- Rm. 301, No. 5 Building, No. 31, Kechuang 7th Street, Beijing Economic-Technological Development Area, Beijing , China | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር:- FTM/ 13273<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበትቀን:- 24/3/2022 | | |
| 3 | ምልክት:- Aulivin | 4 | የምልክቱ መግለጫ:- የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት: ነጭ እና ጥቁር |
| | | 6 | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 5 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>ክትባቶች፤ ለሰብአዊ ዓላማ መድሃኒቶች፤ ለሕክምና ዓላማዎች ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ ለካንሰር ህክምና ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ተያያዥ በሽታዎችን እና እክሎችን ለማከም የመድሃኒት ዝግጅቶች፤ ለሕክምና ወይም ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች የኬሚካል ሪጀንቶች፤ ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች መድሃኒቶች፤ ለህክምና አገልግሎት ተስማሚ የሆኑ የአመጋገብ ንጥረ ነገሮች፤ የሕክምና ዲያግኖስቲክ ሪጀንቶች፤ የደም ምርቶች (ምድብ 5) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከትነውን የንግድ ምልክት ለማስገንዘብ ማመልከቻ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-238-28/8/2014 (6/5/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውም ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም:- SinoCellTech Ltd.<br>የአመልካች አድራሻ:- Rm. 301, No. 5 Building, No. 31, Kechuang 7th Street, Beijing Economic-Technological Development Area, Beijing , China | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር:- FTM/ 13274<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበትቀን:- 24/3/2022 | | |
| 3 | ምልክት:- Ancurlin | 4 | የምልክቱ መግለጫ:- የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት: ነጭ እና ጥቁር |
| | | 6 | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 5 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>ክትባቶች፤ ለሰብአዊ ዓላማ መድሃኒቶች፤ ለሕክምና ዓላማዎች ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ ለካንሰር ህክምና ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ተያያዥ በሽታዎችን እና እክሎችን ለማከም የመድሃኒት ዝግጅቶች፤ ለሕክምና ወይም ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች የኬሚካል ሪጀንቶች፤ ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች መድሃኒቶች፤ ለህክምና አገልግሎት ተስማሚ የሆኑ የአመጋገብ ንጥረ ነገሮች፤ የሕክምና ዲያግኖስቲክ ሪጀንቶች፤ የደም ምርቶች (ምድብ 5) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከትነውን የንግድ ምልክት ለማስገንዘብ ማመልከቻ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-238-28/8/2014 (6/5/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውም ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም:- International Foodstuffs Co. LLC.<br>የአመልካች አድራሻ:- Al-Wahda Street, Industrial Area No. 1 P.O.BOX 4115, Sharjah United Arab Emirates | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር:- FTM/ 13230<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበትቀን:- 7/2/2022 | | |
| 3 | ምልክት:- JINI | 4 | የምልክቱ መግለጫ:- የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት: ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 03 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>የሽንት ቤት ሳሙናዎች፣ ሳሙናዎች፣ ማጽጃ ሳሙናዎች፣ ሻምፖዎች፣ የመዋቢያዎች፣ የቆዳ እና የፀጉር ቅባቶች፣ የቆዳ እና የፀጉር ቅባቶች ሎሽኖች እና ሌሎች በዚህ ክፍል ውስጥ የቆዳ እና የፀጉር እንክብካቤ ምርቶች፣ ፈሳሽ ሳሙናዎች፣ ማጽዳት፣ማቅለሚያ፣ ማሸት እና አብሬዝፍ ዝግጅቶች እና የንፅህና መፍትሄዎች ፣የጽዳት ዝግጅቶች እና ሌሎች የልብስ ማጠቢያዎች ፣ ሽቶዎች (ምድብ 03) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከትነውን የንግድ ምልክት ለማስገንዘብ ማመልከቻ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-238-28/8/2014 (6/5/2022)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውም ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም:- SinoCellTech Ltd.<br>የአመልካች አድራሻ:- Rm. 301, No. 5 Building, No. 31, Kechuang 7th Street, Beijing Economic-Technological Development Area, Beijing , China | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር:- FTM/ 13272<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበትቀን:- 24/3/2022 | | |
| 3 | ምልክት:- Anconrin | 4 | የምልክቱ መግለጫ:- የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት: ነጭ እና ጥቁር |
| | | 6 | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 5 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>ክትባቶች፤ ለሰብአዊ ዓላማ መድሃኒቶች፤ ለሕክምና ዓላማዎች ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ ለካንሰር ህክምና ባዮሎጂካል ዝግጅቶች፤ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ተያያዥ በሽታዎችን እና እክሎችን ለማከም የመድሃኒት ዝግጅቶች፤ ለሕክምና ወይም ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች የኬሚካል ሪጀንቶች፤ ለእንስሳት ሕክምና ዓላማዎች መድሃኒቶች፤ ለህክምና አገልግሎት ተስማሚ የሆኑ የአመጋገብ ንጥረ ነገሮች፤ የሕክምና ዲያግኖስቲክ ሪጀንቶች፤ የደም ምርቶች (ምድብ 5) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከትነውን የንግድ ምልክት ለማስገንዘብ ማመልከቻ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-238-28/8/2014 (6/5/2022)